Amhara Professionals Union– አምባ
info@ambapu.org
www.ambapu.org

# አዲስ አበባ በረራ ናት፤ በረራም አዲስ አበባ

**አምባ የጥናት እና ምርምር ክፍል**

**ነሐሴ 2009 ዓ.ም.**

**ረቂቅ**

በሀቅ ላይ የተመሰረተ ታሪክ ጽኑ የአንድነት መሰረት ነው። ፍትህንም ለማስፈን ወሳኝ ሚና አለው። ታሪክ የራሱ የሆነ የሙያ ስነምግባር አለው። የታሪክ ባለሙያ ለሙያው ፍቅርም ሲል ህይወቱን መስዋዕት ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለበት። የሚያስከፋም ሆነ የሚያስደስት፣ የሚያስነቅፍም ሆነ የሚያስወድስ በመረጃ የተመሰረተ ሀቀኛ ታሪክን መቀበል የስልጡንነት ምልክት ነው። ታሪክን መፍራት፣ መካድ እና ማድበስበስ ኋላቀርነት ነው። ታማኝ መረጃ እስከተገኘ ድረስ ታሪክ ያለምንም ገደብ ይጻፋል። ያስከፋል ወይም ያስነቅፋል ብሎ በታሪክ ላይ ሀጢያት መስራት ጉዳቱ ከባድ ነው። የታሪክ ዕውቀት ያድጋል፣ ይሰፋል ይቀየራል። ይህ የሚሆነው ደግሞ አዳዲስ መረጃዎች በአይነትና በመጠን ሲገኙ ነው።

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነው በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግስት ሚኒስትሮች ምክር ቤት “ኦሮሚያ” የሚባለው ክልል የአገሪቱ ርዕሰ መዲና ከሆነችው ከአዲስ አበባ ስለሚያገኘው ልዩ ጥቅም ያስተላለፈው ረቂቅ አዋጅ ነው። አዋጁ የወጣው የሀገሪቱ “ህገ መንግስት” ስለዚሁ ልዩ ጥቅም ጉዳይ የደነገገውን መሰረት በማድረግ እንደሆነ ተገልጿል። በዚህ ጽሁፍ ለማስገንዘብ የምንሞክረው የዛሬዋ አዲስ አበባ ከ600 ዓመት በላይ ታሪክ እንዳላትና በረራ በመባል በ15ኛው እና 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሆና እንዳገለገለች ነው።

ይህ ጽሁፍ ሁለት አላማዎች አሉት። አንደኛው የበረራን ወይም የአዲስ አበባን የኋላ ታሪክ ከአህመድ ግራኝ (1529-1543) ጦርነት በፊት እና ኦሮሞ ወደ ሸዋ፣ ዳሞት እና ጋፋት ከመስፈሩ በፊት ያለውን ዘመን መዳሰስ ነው። ሁለተኛው ስለ በረራ በኢትዮጵያውያን እና በውጭ ሀገር ጸሓፊዎች የተጻፉ የታሪክ ማስረጃዎችን ለአንባቢ ማስተዋወቅ ነው። በተለይም የቦታው ተወላጆች ስለበረራ በሰጡት ምስክርነት ላይ ተመስርተው የተጻፉትን የጽሁፍ መረጃዎች እና ካርታዎች ለማቅረብ ይሞክራል።

በረራ የኢትዮጵያ የነገስታቱ ዋና መቀመጫ በመሆን ከአጼ ዳዊት ቀዳማዊ (1380-1413) ጀምሮ እስከ አጼ ልብነ ድንግል (1508-1540) ከመቶ ዓመት በላይ አገልግላለች። በረራ ወረብ በሚባል አውራጃ ስር ትተዳደር ነበር። ወረብ ታላላቅ አብያተ ክርስትያናት እና ቤተ መንግስት የነበሩበት በጣም ሀብታም አውራጃ ነበር። በ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ብዙ የውጭ አገሮችን የጎበኙት አባ ዳንኤል የተባሉ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ወረብን በኢየሩሳሌም መስለው ጽፈዋል። በዚሁ ዘመን የግራኝ አህመድን ጦርነት የዘገበው ከሰራዊቱ ጋር በመሆን ወረብንና በረራን ያየው አራብ ፈቂህ ወረብን የሀበሾች ምድራዊ ገነት ይላታል።

ሆኖም ከግራኝ ከ1529 ዓመተ ምህረት ሽምብራ ኩሬ ጦርነት በኋላ የንጉሱ ቤተመንግስት በረራና በወረብ የሚገኙ ታላላቅ አብያተ ክርስትያናት በግራኝ ወታድሮች ተዘርፈዋል፤ ወድመዋል። ከኦሮሞ ፍልሰት በኋላ ደግሞ ወረብና ዋና ከተማው በረራ ብቻ ሳይሆን በሰሎሞናዊያን ዘመን የአገሪቱ የሀይማኖት፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የአስተዳደር እና የህዝብ ማዕከል የነበሩ ቁልፍ ቁልፍ አውራጃዎች በኦሮሞ ቁጥጥር ስር ውለዋል። ከነዚህም ባሌ፣ ፈጠጋር፣ ዳሞት፣ ወረብ፣ ጋፋት፣ ሸዋ እና ጉራጌ ይገኙበታል። ይህም የኢትዮጵያን ፖለቲካ፣ የህዝብ ስብጥር እና አስተዳደር ከግራኝ በበለጠ ሁኔታ እና በዘላቂነት ቀይሮታል።

አጼ ምኒልክ ወደ ወጨጫም ሆነ ወደ እንጦጦ የሄዱበት ምክንያት የአጼ ዳዊትን ከተማ በረራን ፍለጋ ነው። ስለዚህ  አጼ ምኒልክ አዲስ አበባን አልመሰረቱም። ምኒልክ አንድ ስንዝር የኦሮሞ ርስት መሬት አልወሰዱም። የሸዋ መኳንንትም ሆነ አጼ ምኒልክ ወደ እናርያ፣ ወደ አሮጌው ዳሞት እና ጋፋት የዘመቱት አዲስ አገር ለማቅናት አይደለም። ባለ አገሮቹ የጋፋት ዘሮች እና አማሮች ቋንቋቸው ተወልዶ ያደገበትን እና ለብዙ ሺህ አመታት የኖሩበትን አጽመ ርስታቸውን እንደ አዲስ አገር የሚያዩበት ምንም ምክንያት የላቸውም።

ለፍትህ እና ለአንድነት ሲባል በታሪክ ሂደት ጉዳት የደረሰባቸውን ህዝቦች እውቅና መስጠት ከጉዳታቸው እንዲያገግሙ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ድጋፍ ማድረግ ተገቢና ፍትሃዊ ነው። በሃገራችን ኢትዮጵያ የምናየው ግን ከዚህ ተቃራኒ ነው። ርስታቸው የፈለሰባቸው እና ቋንቋቸው የተደመሰሰባቸው ሰዎች ወራሪ ተብለው ዳግም ጉዳት ደርሶባቸዋል። ‘በፊት የበቀለን ጆሮ በኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠው’ እንዲሉ የጋፋት እና የዳሞት ዘሮች፣ ጉራጌዎች  እና አማሮች ቋንቋቸው ተወልዶ ካዳገበት፣ አያቶቻቸውና ቅድመ አያቶቻቸው ትናንት በእየሩሳሌም ከመሰሉት ከጥንት አጽመ ርስታቸው አገራችሁ አይደለም ተብለው ተባረዋል። ለዘላቂ ሰላም እና ፍትህ ሲባል ኢትዮጵያ እንደ አሜሪካና ካናዳ ካሉ አገሮች መማር አለባት።

ሁላችንንም ባለርስት የሚያደርግ በኢትዮጵያዊ ዜግነት ላይ የተመሰረተ ስርዓት እናልም።

## መግቢያ

**ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነው በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግስት ሚኒስትሮች ምክር ቤት "ኦሮሚያ" የሚባለው ክልል የአገሪቱ ርዕሰ መዲና ከሆነችው ከአዲስ አበባ ስለሚያገኘው ልዩ ጥቅም ያስተላለፈው ረቂቅ አዋጅ ነው። አዋጁ የወጣው የሀገሪቱ "ህገ መንግስት" ስለዚሁ ልዩ ጥቅም ጉዳይ የደነገገውን መሰረት በማድረግ እንደሆነ ተገልጿል። በቅርብ ጊዜ ለወጣውም ረቂቅ አዋጅ ሆነ "በህገ መንግስቱ" ለተደነገገው ህግ እንደ ምክንያት የቀረበው የኦሮሞ ህዝብ አዲስ አበባ የተመሰረተችበት መሬት የጥንት ባለቤት ስለሆነ የሚል ነው። አዲስ አበባ ከመባሉ በፊት የመሬቱ የቀድሞ ስም ፊንፊኔ ስለነበረ፤ አዲስ አበባና ፊንፊኔ በአቻነት ለከተማዋ መጠሪያ ስም እንዲሆኑ ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል።[1]**

**ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን ማንሳት እንወዳለን። አንደኛ ፊንፊኔ የሚባል ከተማ በኢትዮጵያም ሆነ በኦሮሞ ታሪክ አይታወቅም፤ እንዲያውም ቃሉ ከኦሮምኛነት ይልቅ አማርኛ ነው።[2] ሁለተኛ የአዲስ አበባ የከተማነትና የመዲናነት ታሪክ የሚጀምረው በዳግማዊ አጼ ምኒልክ (1889-1913) ዘመነ መንግስት አይደለም። አዲስ አበባ ጥልቅ ታሪካዊ መሰረት እና ረጅም የኋላ ታሪክ አላት። በአጼ ምኒልክ ዘመን የተመሠረተችው አዲስ አበባ ቢያንስ የ600 ዓመት የኋላ ታሪክ አላት። የታሪክ መረጃዎች በማያሻማ ሁኔታ እንደሚያሳዩት የአዲስ አበባ እና አካባቢው የጥንት ስም በረራ ይባል ነበር::[3] በመሆኑም የአዲስ አበባ መመስረት የበረራ ዳግም ልደት ተደርጎ መታየት ይኖርበታል። ከ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በሸዋም ሆነ በአጎራባች አውራጃዎች የኦሮሞ ይዞታ አልነበረም። ጥንት በረራና አካባቢው በዘር፣ በታሪክ፣**

[1] አዲስ አበባን የተመለከተው አዋጅ ከዚህ ያድምጡ፡ https://www.youtube.com/watch?v=kRPTjWOHk7s.

[2] ፊንፊኔ ስለሚለው ቃል ጽንሰ-ሀሳብም ሆነ ስርወ-ቃል የአማርኛም የኦሮምኛ መዝገበ ቃላትን መርምረናል። ቃሉን ከአማርኛ መዘገበቃላት ቢገኝም በቅርብም ሆነ ቆየት ባለ ጊዜ ከተጻፉ የኦሮምኛ መዝገበ ቃላት ልናገኘው አልቻልንም። የሚከተሉትን መዝገበቃላት መርምረናል፡ Tilahun Gamta, *Comprehensive Oromo-English Dictionary* (Addis Ababa: Karrayyu Publishing, 2004); E. C. Foot, *A Galla-English, English-Galla Dictionary* (Cambridge: Cambridge University Press, 1913, reprint 1968); Lawrence Tutschek, *Dictionary of the Galla Language* (Munich, 1845); and Karl Tutschek, Lexicon der Galla Sprache (1844); and J. L. Kraf, *Vocabulary of the Galla Language* (London: Church Missionary Society, 1842). ከአማርኛ መዝገበቃላት ውስጥ የሚከተሉትን መርምረናል፡ Dästa Täklä-Wäld, *YäAmarerñña Mäzgäbä Qalat* (Addis Ababa: Artistic Printing press, 1962 Eth. Cal.), 984-990; Thomas Kane, *Amharic Dictionary* (Wiesbaden, Harrassowitz, 1990), 2314; J. Baeteman, *Dictionnaire Amarigna-Français* (Dire-Daoua: Imprimérie Saint Lazare, 1929), 1251; and Kasate Berhan Tasamma, *YäAmarrenna Mazgaba Qalat* (Addis Ababa, 1951 Eth. Cal.),1390.

[3] ስለበራራ የተጻፉትን መረጃወች ከታች በቁጥር 5 ያሉትን የዋቢ ምጽሀፍት ዝርዝር ይመልከቱ (see footnote number 6 below).

**በቋንቋ እና በባህል የተቆራኙት የአማራ፣ የጋፋት እና የጉራጌ ነገዶች ርስት ነበር። ለአዲስ አበባ ተጨማሪ ስም ካስፈለገ በታሪክ ከማይታወቀው ፊንፊኔ ከሚለው ስም ይልቅ በረራ ቢባል የተሻለ ነው። የዚህ ምክንያቱ ታሪካዊ መሰረት ያለው ሰለሆነ እና የአዲስ አበባን ኗሪ ህዝብ የከተማዋን ሀቀኛ ታሪክ ለማወቅ እና ታሪካዊ ቅርሶቿንም ለመጠበቅ እንዲነሳሳ ስለሚረዳ ነው።**

**ህጉ የወጣው ለወቅታዊ ፖለቲካ ፍጆታ ሲባል እንደሆነ ግልጽ ነው። በኢትዮጵያ ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል ታሪክን መስዋዕት ማድረግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተለመደ ሆኗል። ታሪክን መካድ፣ የተደረገውን አልተደረገም፣ ያልተደረገውን ተደርጓል ማለት የኢትዮጵያ ምልክት ከሆነ ውሎ አድሯል። የኢትዮጵያ የጎሳ ፖለቲከኞች በሺዎች ዓመታት የሚቆጠረውን የሀገራቸውን ታሪክ ቆራርጠው በመቶ አመት ወስነውታል። ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከርሳቸው በፊት የነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታት ያላስተዳደሩትን አንድ ጋት አዲስ መሬት አላመጡም። በአገሪቱ ያለው የውሸት ዳመና በታሪክ ተማሪዎች ላይም ከባድ ተጽኖ አሳድሯል። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የታሪክ ምሁራን ሳይቀሩ ከፖለቲካ ሰዎች ያልተናነሰ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ኃጢአት ሲሰሩ ማየት የተለመደ ነው። ታሪክ ለፖለቲካ ጥቅም ሲውል ጉዳቱ በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ኢትዮጵያ ወስጥ በአለፉት 40 ዓመታት የተከሰቱት እና አሁንም እየተከሰቱ ያሉት ግጭቶች የፈጠራ ወሬ እና የተዛባ የታሪክ ትንታኔ ድምር ወጤቶች ናቸው ማለት ይቻላል።ለምሳሌ ከሺህ ዓመታት በላይ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረው እና ትናንት ራስ አሉላ ሲያስተዳድሩት የነበረው ባህረ-ምድር (ያሁኑ ኤርትራ) የኢትዮጵያ ቅኝ ነው ተብሎ ራሱን የቻለ ሀገር ለመሆን የበቃው ታሪክ በመዛባቱ ምክንያት ነው። ባጭሩ የኢትዮጵያ ዘርፈ-ብዙ ችግር ባብዛኛው የታሪክ ክህደት ወይም ውሸት የፈጠረው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።**

**ታሪክ የራሱ የሆነ የሙያ ስነምግባር ያለው መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል። የታሪክ ተማሪ ለሙያው ፍቅርም ሲል ህይወቱን መስዋዕት ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለበት። የሚያስከፋም ሆነ የሚያስደስት፣ የሚያስነቅፍም ሆነ የሚያስወድስ በመረጃ የተመሰረተ ሀቀኛ ታሪክን መቀበል የስልጡንነት ምልክት ነው። ታሪክን መፍራት፣ መካድ እና ማድበስበስ ኋላቀርነት ነው። ታማኝ መረጃ እስከተገኘ ድረስ ታሪክ ያለምንም ገደብ ይጻፋል። ያስከፋል ወይም ያስነቅፋል ብሎ ታሪክን ሆን ብሎ ማዛባት ጉዳቱ ከባድ ነው። የታሪክ ዕውቀት ያድጋል፣ ይሰፋል ይቀየራል። ይህ የሚሆነው ደግሞ አዳዲስ መረጃዎች በአይነትና በመጠን ሲገኙ ነው። ታሪክ የለውጥ ሂደት መሆኑን መቀበል አስፈላጊ ነው። ወደኋላ እያዩ ወደፊት መራመድ አይቻልም። የታሪክ እውቀት በድካም በልፋት**

**የሚገኝ ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ ያለምንም ድካም የሚገኝ ሳያውቁ አዋቂ የሚባሉበት ሙያ ቢኖር ታሪክ ነው ማለት ይቻላል። የታሪክ ምሁሩም፣ ጋዜጠኛውም፣ ካድሬውም፣ ዘፋኙም፣ ሀኪሙም፣ የቋንቋ አስተማሪውም፣ መሃንዲሱም ሆነ የሃይማኖት ሰባኪው እኩል የታሪክ ባለሙያዎች ናቸው።**

**የዚህ ጽሁፍ አርስተ ጉዳይ ወደ ሆነው ወደ አዲስ አበባ የኋላ ታሪክ እንመለስ። የአዲስ አበባ የጥንት ስም በረራ ነው ብለናል። በረራም የኢትዮጵያ የነገስታቱ ዋና መቀመጫ በመሆን ከአጼ ዳዊት ቀዳማዊ (1380-1413) ጀምሮ እስከ አጼ ልብነ ድንግል (1508-1540) ከመቶ ዓመት በላይ አገልግላለች። በረራ ወረብ በሚባል አውራጃ ስር ትተዳደር እንደ ነበር የታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ። ወረብ ታላላቅ አብያተ ክርስትያናት እና ቤተ መንግስት የነበሩበት በጣም ሀብታም አውራጃ ነበር። በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ብዙ የውጭ አገሮችን የጎበኙት አባ ዳንኤል የተባሉ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ ወረብን በኢየሩሳሌም መስለው ጽፈዋል።[4] በዚሁ ዘመን የግራኝ አህመድን ጦርነት የዘገበው ከሰራዊቱ ጋር በመሆን ወረብንና በረራን ያየው ሺሀብ አደዲን አህመድ ቢን አብደል ቃድር ቢን ሳሌም ቢን ኡትማን (**Šihāb ad-Dīn Aḥmad bin Abd al-Qāder bin Sālem bin Uṯmān) ***ፉቱሕ አል-ሀበሻ* (*Futūḥ al-Ḥabaša*) በተሰኘው መጽሀፉ ወረብን የሀበሾች ምድራዊ ገነት ይላታል።[5] ሺሀብ አደዲን በደንብ የሚታወቀው አረብ ፈቂህ በሚባለው ቅጽል ስሙ ነው። እኛም ይኸን ተከትለን በዚህ ጽሁፍ በቅጽል ስሙ እንጠራዋለን።**

4 የዚህ ምንጭ የኦሮሞ ትውልድ ያላቸው የጎጃሙ ታሪክ ጸሃፊ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ናቸው። መረጃው የተገኘው ከሚከተለው መጽሀፋቸው ነው፡ "የዘመን ታሪክ ማጠራቀሚያ"፡ ያልታተመ የእጅ ጽሁፍ፡ ብሄራዊ ቤተ መፅሀፍ 382/63 (አዲስ አበባ)› ገጽ 77. መጽሀፉ የጎጃምን ህዝብ የዘር ሀረግ ይዘረዝራል። አሁን የሚገኘው ብሄራዊ ቤተ መጽሀፍ ነው። ብሄራዊ ቤተ መጽሀፍ ለምን የዘመን ታሪክ ማጠራቀሚያ እንዳለው አልገባንም። ከዚህ ከጠቀስ ነው ገጽ አለቃ የሚከተለውን ጽፈዋል፡ "ከዚህ በኋላ ደግሞ አባ ዳንኤል የሚባሉ መነኩሴ በምናኔ ምክንያት አለሙን ሁሉ እየዞሩ እንዲህ ብለው ጽፈዋል "ምጣኔ ሀገር ዘጸሀፈ አባ ዳንኤል ዘሀገረ እንቆይ አቡሆሙ ለቴዎድሮስ ወለዘርዓ ያዕቆብ ነገስታተ ኢትዮጵያ ህንደኪ ከመአዳል ባቢሎን ከመደዋሮ ወባሊ ፋርስ ከመፈጠጋር አርማንያ ከመጽላልሽ ሚይን ከመ ተጉለት ሶርያ ከመዘርቦች ኢየሩሳሌም ከመወረብ። ሮም ከመ እንደገብጦን። ጽርዕ ከመ ዳቢ ጎግ ማጎል ከመ ሙገር። ግብጽ ከመገንዝ ወገሞ አፍርንጅ ከመሺሜ ወጋፋት መንግስተ ሰማይ ከመ ጎጃም" ብለው ያገር አምሳያ ጽፈዋል። ይኸውም ዲማ ጊዮርጊስ የሚባል አገር ይገኛል።"

5 Šihāb ad-Dīn Aḥmad bin Abd al-Qāder bin Sālem bin Uṯmān, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia, [16th century]*, edited and translated by Paul Stenhouse (Hollywood: Tsehai Publishers, 2003), 169.

## የጽሁፉ ዓላማ

**ይህ ጽሁፍ ሁለት አላማዎች አሉት። አንደኛው የበረራን ወይም የአዲስ አበባን የኋላ ታሪክ ባጭሩም ቢሆን ለመዳሰስ ነው። የጽሁፉ ትኩረት ከአህመድ ግራኝ (1529-1543) ጦርነት በፊት እና ኦሮሞ ወደ ሸዋ፣ ዳሞት እና ጋፋት ከመስፈሩ በፊት ስላለው ዘመን ነው። ሁለተኛው ስለ በረራ በኢትዮጵያውያን እና በውጭ ሀገር ጸሓፊዎች የተጻፉ የታሪክ ማስረጃዎችን ለአንባቢ ለማስተዋወቅ ነው። በተለይም የቦታው ተወላጆች ስለበረራ በሰጡት ምስክርነት ላይ ተመስርተው የተጻፉትን የጽሁፍ መረጃዎች እና ካርታዎች ለማቅረብ ይሞክራል። የበረራን ታሪክ ያጠኑ ምሁራን ከብዙ በጥቂቱ ኦ.ጅ. ኤስ. ክራውፎርድ (O.G.S. Crawford)፣ ሪቻርድ ፓንክረስት እና ሀርትዊግ ብርተንሪዝ ባንድነት (Richard Pankhurst and Hartwig Breternitz)፣ ሳሙኤል ወከር (Samuel Walker) እና ማርኮ ቪጋኖ (Marco Vigano) ይገኙበታል።[6] ከታች እንደምናየው በተጨማሪም እውቁ ጣሊያናዊ የካርታ ባለሙያ ፍራ ማውሮ (Fra Mauro) በረራን እና በአካባቢው ያሉትን ከተሞች፣ ወንዞች፣ ተራሮች እና ገዳማት በ1450 ዓመተ ምህረት ባዘጋጀው የአለም ካርታ መሬት ላይ ካለው እውነት ምንም ሳያፋልስ የቦታውን ተወላጆች በመጠየቅ አስፍሯቸዋል። የፍራ ማውሮ የአለም ካርታ በትክክለኛነቱ በአለም የተደነቀ ነው። ካርታው አውሮፓውያን ኢትዮጵያን ጨምሮ አለምን ለማሰስ በዘመኑ ባደረጉት ጥረት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ፍራ ማውሮ ለሳይንስ እውቀት እድገት ላደረገው አስተዋጾ እውቅና ለመስጠት የጨረቃ የተወሰኑ አካላት በስሙ ተሰይመውለታል።[7]**

**የዚህ ጽሁፍ ይዘት ያልነበረን ወይንም ያልተነገረን አዲስ ታሪክ ለማስተዋወቅ አይደለም። ለዚህ ጽሁፍ የተጠቀምናቸው መረጃዎችም አብዛኞዎቹ ከዚህ በፊት ስለ በረራ ታሪክ በጻፉ ሰዎች የታወቁ ናቸው። ነገር ግን ከዚህ በፊት በምሁራን ያልተዳሰሰ ለታሪኩ በቦታም በዘመንም ቅርብ**

---

[6] O.G.S. Crawford, ed., *Ethiopian Itineraries ca. 1400-1524* (Cambridge University Press for the Haklyut Society, 1955); Harwig Breternitz and Richard Pankhurst, "Barara, the royal city of 15th and early 16th century (Ethiopia): medieval and other early settlements between Wechecha Range and Mt Yerer: results from a recent survey," *Annales d'Ethiopie* 24 (2009), 209-249; Marco Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped Central Shoa on the Fra Mauro map, is significant lost medieval Ethiopia recovered?", A paper for the Act Book of the "Exploring Ancient China's Links to Africa" meetup, Addis Ababa, Oct. 29-31 2014; and Samuel Walker, The Lost Cities of Ethiopia, Popular Archaelogy 27 (2017): http://popular-archaeology.com/issue/summer-2017/article/the-lost-cities-of-ethiopia acessed 7/31/2017).

[7] Surekha Davies, "The Wondrous East in the Renaissance Geographical Imagination: Marco Polo, Fra Mauro and Giovanni Battista Ramusio," *History and Anthropology* 23: 2(2012), 217-222 and Piero Falchetta, *Fra' Mauro's World Map: With a Commentary and Translations of the Inscriptions* (Turnhout: Brepols Publishers, 2006); and "Fra Mauro Map," *Wikipedia, the free encyclopedia* (https://en.wikipedia.org/wiki/Fra_Mauro_map).

የሆነ የታሪክ ማስረጃ ተጠቅመናል።[8] የበረራን ታሪክ የጻፍነው አንዱን መጤ እና እንግዳ፣ አንዱን ተወላጅ እና ነባር ለማድረግ አይደለም። ጽሁፉን ለማዘጋጀት ያስፈለገበት ምክንያት ስለአዲስ አበባ የኋላ ታሪክ ያለውን የመረጃ ክፍተት በተወሰነ ደረጃ ለመድፈን ይጠቅማል ብለን ስላመንን እና ስለቦታው ታሪክ ኢትዮጵያውያን ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።

## የጽሁፉ ክፍሎች

ይህ ጽሁፍ በአራት (4) አጫጭር ክፍሎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ክፍል በረራ ከመመስረቷ በፊት የነበረውን የታሪክ ሂደት ባጭሩ ይዳስሣል። በዚህ ክፍል በበረራና በአካባቢው ይኖሩ ስለነበሩ ነባር ህዝቦች ወይም ተወላጆች ታሪክ እንዲሁም ስለኢትዮጵያ መንግስትና የክርስትና ሃይማኖት መስፋፋት ባጭሩ ይቀርባል። ሁለተኛው እና ዋናው በረራ ከተመሰረተችበት ከአጼ ዳዊት (1380-1413) ዘመነ ምንግስት ጀምሮ ከተማው በግራኝ ሰራዊት ተዘርፎ እስከወደመበት እስከ 1530 ዓመተ ምህረት ያለውን ታሪክ ይሸፍናል። በዚህ ክፍል የቀረበው አብዛኛው ሀተታ የበረራ ትክክለኛ መገኛ የት እንደነበረ በምሁራን የተሰጡ ትንታኔዎችን እና ስለከተማው የአይን ምስክሮች የተናገሩት እና የጻፉት የጽሁፍ መረጃ ነው። ሶስተኛው ክፍል ከ10 ዓመት በፊት በእንጦጦ ማርያም አቅራቢያ ስለተገኘው የጥንት ከተማ በተለይም የፔንታገን ቅርጽ ስላለው ባለ12 የመመልከቻ ማማ የመከላከያ ግንብ እና ቤተ መንግስት ታሪክ ያትታል። ይህ ክፍል በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመን በታውን የጎበኙ የአውሮፓ ወታደራዊ ባለሙያዎች ስለመከላከያ ግንቡ የሰጡትን አስተያየትም አካትቷል። በተጨማሪም የከርሰ ምድር፣ የቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ ባለሙያዎች ስለግንቡ አሰራር የሰጡትን ሙያዊ አስተያየት በዚሁ ክፍል ቀርቧል። አራተኛውና የመጨረሻው ክፍል የበረራን ታሪክ ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ማለትም ከ1529 ዓመተ ምህረት ጀምሮ አጼ ምኒልክ አዲስ አበባን እስከ መሰረቱበት ወይም እስከ በረራ ዳግም ልደት ያለውን ዘመን ታሪክ ያካትታል። ይህን ጽሁፍ አንባቢ እንደፈለገ ሊያነበው ይችላል። የበረራን ታሪክ ብቻ ማወቅ ለሚፈልግ ሁለተኛውን እና ሶስተኛውን ክፍል ብቻ ማንበብ በቂ ነው። ኦሮሞ በበረራ አካቢቢ ከሰፈረ ጀምሮ እስከ አዲስ አበባ አመሰራረት ያለውን ብቻ ማወቅ ለሚፈልግ 4ኛውን ክፍል ብቻ ማንበብ ይቻላል። አንባቢ ጊዜ ወስዶ ሁሉንም ክፍሎች ቢያነብ የተሻለ ግንዛቤ ይሰጣል

[8] *ድርሳነ ዑርኤል በግዕዝና በአማርኛ፡ መልክአ ዑርኤል በልሳነ ግዕዝ* [*Dersana Urael BaGeez Ena BaAmarigna, Malke'a Urael belesana Geez*](Addis Ababa, 1985 Eth. Cal.).

እንላለን ። አንዱን ክፍል አንብቦ ሌላውን መተው ለአንባቢው ስለ በረራ ታሪክ ሙሉ ስዕል አይፈጥርለትም።

በመጨረሻም ምንም እንኳ ሌሎች ኢትዮጵያውያንም በከተማው እንደሚኖሩ ባያጠያይቅም የአማራ፣ የጉራጌ እና የጋፋት ህዝብ ከበረራ ጋር የተለየ ቁርኝት ያላቸው ሆኖ አግኝተነዋል። ስለዚህ ጉራጌን፣ ዳሞትን፣ ጋፋትን እና ሸዋን ደጋግመን የምናነሳበት ምክንያት ስለ በረራ እና ተዛማጅ ጉዳዮች የተጻፉ የታሪክ መረጃዎች ስላስገደዱን ብቻ ነው። በሰለሞናውያን ነገስታት ዘመን (1270-1530) የተጻፉት መረጃዎች ጉራጌን ጠቅሰው፤ ጋፋትን፣ ዳሞትን እና ሸዋን ሳይጠቅሱ አያልፉም ማለት ይቻላል። ጋፋት፣ አማራ እና ጉራጌ የደቡብ ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ናቸው። ለብዙ ሽህ ዓመታት አብረው ኖረዋል። በመካከላቸው ስላለው የቋንቋና የባህል መመሳሰል ቀጥሎ ባለው ክፍል ቀርቧል። ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ጽሁፍ የተጠቀምነው የአውሮፓውያንን የዘመን አቆጣጠር ነው። ጽሁፉ ጊዜ ተውስዶ ቢዘጋጅ ብዛት ያላቸው ተጨማሪ መረጃዎች ማግኘትና ማካተት እንደሚቻል እየጠቆምን፣ መካተት ሲገባቸው የተዘለሉ መረጃዎች ቢኖሩ ጽሁፉን ለማዘጋጅት የነበረን ጊዜ አጭር በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ አንባቢ እንዲረዳልን እንጠይቃለን።

## ቅድመ በረራ የኢትዮጵያ ታሪክ ባጭሩ


ከላይ እንደጠቀስነው በበረራ እና አካባቢው የአማራ፣ የጋፋት እና የተለያዩ የጉራጌ ቋንቋ ተናጋሪዎች ይኖሩ ነበር። ሁሉም ሴማዊ ተብሎ ከሚታወቀው ንዑስ የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባሉ። የሴማዊ ቋንቋዎች ደግሞ አፍሮ-እስያዊ (Afroasiatic) ከሚባለው ትልቅ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ ይመደባሉ። አፍሮ-እስያዊ በዓለም ካሉ ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰቦች ውስጥ በአራተኛ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን በውስጡ ሶስት መቶ ሚሊዮን ሰዎች የሚናገሯቸው 375 ህያዋን ቋንቋዎችን ያቀፈ ነው። ስያሜውንም ያገኘው በአፍሪካ ብቻ ከሚነገሩት በተጨማሪ በአፍሪካም በእስያም የሚነገሩ ሴማዊ ቋንቋዎች በውስጡ ስለያዘ ነው። ከነዚህም ውስጥ አረብኛ፣ ዕብራይስጥ፣ አካድያኛ (የጥንት ባቢሎናውያን ቋንቋ)፣ አራማይክ(የኢየሱስ ክርስቶስ የአፍ መፍቻ ቋንቋ)፣ ግዕዝ፣ ትግርኛ፣ አማርኛ እና የጉራጌ ቋንቋዎች ይገኙበታል።[9]

[9] Zygmunt Frajzyngier and Erin Shay, “Introduction,” in *The Afroasiatic Languages* (Cambridge: Cambridge University Press, 2012), 1-17.

**የቋንቋ  የቅድመ-ታሪክ እና የታሪክ ምሁራን ለሁለት መቶ ዓመታት ስለአፍሮ-እስያዊ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች መነሻ እና ለዓለም ስልጣኔ ስላደረጉት አስተዋጽኦ ሰፊ ጥናት እና ምርምር አድርገዋል። ከነዚህም ውስጥ ማርቲን በርናል (Martin Bernal) እና ክርስቶፈር ኤኽረት (Christopher Ehret) ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው።[10] ስለሴማዊም ሆነ በአጠቃላይ ስለ አፍሮ-እስያዊ ቋንቋዎች መነሻ እና እድገት የተለያዩ አስተያየቶች ተሰጥተዋል። በመረጃ የተደገፈው እና በምሁራን ዘንድ በሰፊው ተቀባይነት እያገኘ ያለው አስተሳሰብ ግን የአፍሮ-እስያዊ ቋንቋዎች መነሻ አፍሪካ በተለይም ደቡብ ኢትዮጵያ እንደሆነ ነው። የዚህ አስተሳሰብ ዋና አቀንቃኞች ማርቲን በርናል እና ሮጀር ብሌንች (Roger Blench) ናቸው። ማርቲን እንደሚለው ከሆነ በአፍሮ-እስያዊ ውስጥ ለሚገኙት የተለያዩ ቋንቋዎች መነሻ የሆነው የመጀመሪያው ቋንቋ (Proto-Afroasiatic) ተናጋሪዎች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ከደቡብ ኢትዮጵያ ተነስተው ወደ ሰሃራ በርሃ፣ ወደ ሰሜን አፍሪካ እና ግብጽ፣ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ እና ደቡብ አረቢያ እንዲሁም የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የተለያዩ አካባቢዎች ፈልሰዋል። በአፍሮ-እስያዊ ውስጥ የሚገኙት ንዑስ የቋንቋ ቤተሰቦች ማለትም የበርበር፣ የቻድ፣ የግብጽ፣ የኩሽ፣ የኦሞ እና የሴማዊ ቋንቋዎች (Berber, Chadic, Egyptian, Cushitic, Omotic, Semitic) የዚህ ፍልሰት ውጤት ናቸው (ካርታ 1ን ይመልከቱ)። ይህ የሆነው ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ10ኛው ሺህ እና በ9ኛው ሺህ ዘመን ነው።[11]**

[10] Martin Bernal, *Black Athena: The Afroasiatic Roots of Classical Civilization: The Fabrication of Ancient Greece 1785-1985* vol.1 (New Brunswick: Rutgers University Press, 1987); *idem, Black Athena The Afroasiatic Roots of Classical Civilization* vol. 3 (New Brusnwick: Rutgers University Press, 2006); and Christopher Ehret, *Reconstructing Proto-Afroasiatic (Proto-Afrasian): Vowels, Tone, Consonants, and Vocabulary* (Los Angeles: University of California, 1995).

[11] Bernal, *Black Athena* vol.1, 11; and *idem*, *Black Athena* vol. 3, 58-89; Roger Blecher, *Language, Archaelogy and the African Past* (Cambridge, AltaMira Press, 2006), 82-98.




**ካርታ 1. From Blench, Roger Blench, *Arachaelogy, Language and the African Past*, 96.**

**ወደ ሴማዊ ቋንቋዎች ስንመለስ ለረጅም ጊዜ ደቡብ አረቢያ የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች መነሻ ተደርጎ ይቀርብ የነበረው አሁን ተቀባይነት የለውም። ሁሉም የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች ተወልደው ያደጉት ከዚሁ ከኢትዮጵያ በተለይም ደቡብ ኢትዮጵያ እንደሆነ የቋንቋ ምሁራን ይስማማሉ። ለዚህ ደግሞ ሁለት ምክንያቶች አሉ። አንደኛው ኢትዮጵያ ያሉት የሴማዊ ቋንቋዎች ብዛት ነው። ኢትዮጵያ ከሌላው አለም በላይ ህያዋን ሴማዊ ቋንቋዎች የሚገኙባት አገር ናት። የቋንቋ ብዙህነት ደግሞ የለውጡ ሂደት የሚፈጀውን የጊዜ ጥልቀት፣ ማለትም የአነሳስ ቀደምትነትን ወይም ጥንታዊነትን ያመለክታል (greater language diversity shows greater time depth)። ስለሴማዊ ቋንቋዎች ብዙነት ስናነሳ፣ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ 16 ሴማዊ ቋንቋዎች ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ 13 የሚሆኑት በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም በሸዋ እና በጥንቱ የዳሞት አውራጃ ይነገሩ ነበር። ከ13ቱ የደቡብ የሴም ቋንቋዎች 7 የሚሆኑት በጉራጌኛ ቋንቋ ይጠቃለላሉ። ሁለተኛው ምክንያት በኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች በተለይም ደግሞ በጉራጌ ቋንቋዎች ውስጥ የሚስተዋለው የስርዓት/የቅርጽ የጥንታዊነት ባሕሪ (archaism) ነው።[12]**

---

[12] Girma A. Demeke, *The Origin of Amharic* 2nd ed. (Trenton: The Red Sea Press, 2009), Chap 5; *idem*, "The Ethio-Semitic Languages (Re-examining the Classification)," *Journal of Ethiopian Studies* 34: 2 (2001), 60-70; Grover Hudson, "*Ethiopian Semitic archaic heterogeneity*, *Ethiopian Studies at the Millenium,"* in Proceedings of the 14th International Conference of Ethiopian Studies, Baye Yimam et al, eds., 1765-1776 (Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies); *idem*, Grover Hudson, *Northeast African Semitic-Lexical Comparisons and Analysis* (Wiesbaden: Otto Harrassowitz Verlag, 2013), 1-2 and 8; Martin Bernal, 'A New Proto-Semitic," Paper given at the tenth annual North American Conference of Afroasiatic Linguistics,

**የቋንቋ ምሁራን የኢትዮጵያን እና የኤርትራን ሴማዊ ቋንቋዎች የሰሜን ሴማዊ ቋንቋዎች (northern Semitic languages) እና የደቡብ ሴማዊ ቋንቋዎች (southern Semitic languages) ብለው በሁለት ይከፍሏቸዋል። የሰሜን ሴማዊ ቋንቋዎች የሚባሉት ግዕዝ፣ ትግረ እና ትግርኛ ሲሆኑ አማርኛን ጨምሮ የተቀሩት ሴማዊ ቋንቋዎች ደግሞ በደቡብ ሴማዊ ቋንቋዎች ይጠቃለላሉ። ከላይ እንዳየነው ለሰሜኑም ሆነ ለደቡቡ ሴማዊ ቋንቋዎች ወላጅ ቋንቋ (proto-Ethiopian Semitic language) ይነገር የነበረው አሁን የጉራጌ ቋንቋዎች የሚገኙበት አካባቢ ነው። የዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከጉራጌ አካባቢ ተነስተው ወደ ሰሜን እና ደቡብ አቅጥጫ ፈልሰው የየራሳቸው ቅርጽ እና ይዘት ያላቸው ሴማዊ ቋንቋዎች ተናጋሪ ለመሆን በአጠቃላይ አምስት ሽህ አመት ወስዶባቸዋል ተብሎ ይገመታል።[13] ከሁሉም ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች የአማርኛ ተናጋሪዎች በሁሉም አቅጣጫ የተንቀሳቀሱ ሲሆን የሚኖሩበትም መሬት በዚሁ ምክንያት በጣም ሰፊ እንደነበረ የሚታወቅ ነው። በሌላ አነጋገር የአማርኛ ተናጋሪ ህዝብ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ከደቡብም ሆነ ከሰሜን ሴም እና የኩሽ ነገዶች ጋር ሰፊ እና ጥብቅ ትሥሥር ያለው ህዝብ ሆኖ ተገኝቷል። ምንም እንኳ ከደቡብ ሴማዊ ቋንቋዎች ቢመደብም የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሰሜን ኢትዮጵያ (ላስታ፣ አንጎት፣ ወለቃ፣ አምሀራ) እና በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ (ጎጃምና በጌምድር) በስፋት ይኖሩ ነበር፤ አሁንም ይኖራሉ።[14] የአማርኛ ተናጋሪዎችም ከአገው፣ ከትግሬና ከግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ጋር ለብዙ ሽህ አመታት አብረው ኖረዋል፤ በደምም ተዋህደዋል። የአገው፣ የግዕዝ፣ የአማርኛ እና የትግርኛ ቋንቋዎች እና ተናጋሪዎች ታሪካዊ ትስስር እና ግንኙነት በሰፊው የተጠና እና የተነገረ ስለሆነ ከዚህ መድገም አያስፈልግም። አማርኛ ከደቡብ ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር ያለው ትስስር ግን ብዙም አይታወቅም ማለት ይቻላል።**

**የቋንቋዎች መቀራረብ ወይም መራራቅ የሚታወቀው ቋንቋዎቹ በሚጋሯቸው የድምጽ፣ የስነ-ምእላድና የሰዋስው ስርዓቶች (morphology and syntax)፣ እንዲሁም የየቋንቋዎቹ ተናጋሪዎች አንዱ የሌላውን ንግግር በሚረዱበት መጠን (mutual intelligibility) ተጠንቶ ነው።**

---

Boston (1980). However, Martin seems to have revised his original thesis about the orgin of the Semitic languages in his most recent book *Black Athena The Afroasiatic Roots of Classical Civilization* vol 3 (New Brusnwick: Rutgers University Press, 2006), 15, 82-83.

[13] Girma, *The Origin of Amharic,* 123-127; *idem*, "The Ethio-Semitic Languages," 59-70; and Hudson, *Northeast African Semitic-Lexical Comparisons and Analysis,* 36-52; *idem*, "Ethiopian Semitic Overview," *Journal of Ethiopian Studies* 33: 2 (2000), 75-86.

[14] Girma, *The Origin of Amharic,* Chapter 6.

**ቋንቋዎቹ ከሚጋሯቸው ቃላት አኳያ አማርኛ ከአርጎብኛ ቋንቋ ጋር እጅግ በጣም ተመሳሳይ እንደሆነ ስለአማርኛ ቋንቋ ሰፊ ጥናት ያደረገው ግርማ አውግቸው በአጽንዖት ጽፏል። በዚህም የተነሳ አንዳንድ የቋንቋ ምሁራን አርጎብኛን የአማርኛ ዳይሌክት (dialect [ዘየ]) እስከ ማለት ደርሰው ነበር። ግርማ እንደሚለው አማርኛ እና አርጎብኛ የተለያዩት በቅርብ ጊዜ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን የለያቸውም ሀይማኖት ነው።[15] ታሪኩ እንዳይሰፋና ከጽሁፉ አላማ ጋር ብዙ ግንኙነት ስለሌለው የአርጎባን እና የአማራን ታሪካዊ ትስስር በዚህ ጽሁፍ አላካተትነውም። የቋንቋዎቹ የቃላት ተመሳሳይነት ጥናት እንዳመለከተው ጋፋትኛ እና አማርኛ 65 በመቶ፣ አማርኛ እና ክስታኔ 66 በመቶ፣ ጋፋትኛ እና ክስታኔ 62 በመቶ ተመሳሳይነት አላቸው።[16] ግርማ የዴቪድ አፕልያርድ (David Appleyard) እና የሌሎችን የቋንቋ ምሁራን ስራዎች በመጥቀስ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦሮሞ ፍልሰት በፊት አማርኛ ወይም የአማርኛ-አርጎብኛ ቀዳሚ/አባት ቋንቋ (Proto-Amharic-Argobba) ከሀረር ጀምሮ እስከ ዝዋይ ሀይቅ አካባቢ፣ ሸዋ፣ ዳሞት እንዲሁም ባሌ ድረስ ይነገር እንደነበረ ጽፏል።[17] ባጠቃላይ ከላይ የቀረበው የቋንቋ መመሳሰል የሚያሳየው አርጎባ፣ ጉራጌ፣ ጋፋት እና አማራ የአንድ አባት ልጆች መሆናቸውን ነው። ሁሉም ካንድ ምንጭ የተቀዱ ጥንታዊ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝቦች ናቸው።**

**ከላይ ባጭሩም ቢሆን የቀረበው የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎች ዘገምተኛ ለውጥ (evolutionary change) ለማወቅ የተቻለው በታሪካዊ ስነልሳን ንጽጽራዊና መልሶ የማዋቀር ዘዴ የተገኙ መረጃዎችን በመጠቀም ነው። ታሪካዊ ስነልሳን (historical linguistics) የጽሁፍ መረጃ ባልነበረበት ዘመን የቋንቋዎችን የለውጥ ሂደት ለማጥናት ያስቻለ የጥናት ዘርፍ ነው። ተጨማሪ የጽሁፍ መረጃ ለማግኘት የተቻለው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ህዝቦች በመንግስት ደረጃ መተዳደር ሲጀምሩ ነው። የኢትዮጵያ የመንግስት አስተዳደር፣ የኃይማኖት፣ የባህል፣ የስነ ጽሁፍ እና ስልጣኔ መሰረት የተጣለው ከክርስቶስ ልድት በፊት ከ1000 ዓመተ ዓለም ጀምሮ እስከ 1300 ዓመተ ምህረት ባሉት 2300 ዓመታት እንደ ሆነ በአክሱም አካባቢ ለረጅም ጊዜ ቁፋሮ ያደረገው እውቁ እንግሊዛዊ አርኬዎሎጅስት ዴቪድ ፊሊፕሰን (David Phillipson) በቅርብ ጊዜ በጻፈው መጽሀፉ ያስረዳል። የዳማት መንግስት (450 ዓመተ ዓለም)፣ የአክሱም መንግስት (ከ100-700 ዓመተ**

[15] Girma, *The Origin of Amharic*, 132-142.
[16] Hudson, *Northeast African Semitic-Lexical Comparisons and Analysis*, 32.
[17] Girma, *The Origin of Amharic*, 129-135.

**ምህረት) እና የዛግዌ ስርወ መንግስት (1000-1270 ዓመተ ምህረት) ተወልደው ያደጉት በዚኹው ዘመን ነበር።**

**ከ700 ዓመተ ምህረት ጀመሮ የኢትዮጵያ ነገስታት ዋና መቀመጫቸውን ከአክሱም ወደ ላስታ እና አምሀራ አካባቢ አዛውረውት ነበር። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ቀይ ባህር እና በዙሪያው ያሉ አካባቢዎች በአረቦች ቅጥጥር ስር በመዋላቸው እና ቤጃ የሚባሉት ገባር ህዝቦች ስላመጹ ነው።[18] የማዕከላዊ መንግስቱ መቀመጫ አንጻራዊ ሰላም ወደላበት ወደ ላስታ እና ወደ አምሀራ መዛወሩ ደግሞ መጀመሪያ የዛግዌን ቀጥሎ የሰለሞናውያንን ወደ ሥልጣን መምጣት ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል ማለት ይቻለል። በ1270 ዓመተ ምህረት የመንግስት ስልጣን በሰለሞናውያን ነገስታት እጅ ገባ። የሰለሞናዊ ስርዎ-መንግስት መስራች አጼ ይኩኖ አምላክ (1270-1285) ሲሆኑ ተወልደው ያደጉት አምሀራ ነው። በዚህም ምክንያት ለሚቀጥሉት 300 ተከታታይ ዓመታት የአማራ አካባቢዎች (በተለይም ደግሞ ሸዋ እና ቤተ አምሀራ) የኢትዮጵያ የባህል፣ የኃይማኖት፣ የፖለቲካ እና ወታደራዊ ኃይል ማዕከል ለመሆን ቻሉ።**

**በዛግዌ ነገስታት ዘመን አማራ እና ሸዋ ከማዕከላዊ መንግስት ጋር ያላቸው ቁርኝት ተጠናክሮ ቀጠለ። የአማርኛ ቋንቋ "ልሳነ ንጉስ" የተባለው ከአጼ ላሊበላ ዘመነ ምንግስት ጀምሮ እንደሆነ የታሪክ ተመራማሪው ስርግው ሀብለ ሥላሴ ጽፈዋል። ይህም ለአጼ ይኩኖ አምላክ ወደ ስልጣን መምጣት ረድቷቸዋል። በተጨማሪም ይኩኖ አምላክ ከአክሱሙ የመጨረሻ ንጉሥ ከአጼ ድል ነዓድ በቀጥታ ሥለሚወለዱ ወደስልጣን የመጡትም በዘር ሀረጋቸው ምክንያት የመንግስት ስልጣን ይገባኛል ብለው ስላመኑ የመጨረሻውን የዛግዌ ንጉስ ይትባረክን በ1270 ዓመተ ምህረት በተደረገ ጦርነት በማሸነፍ ነው። በመጨረሻም ይኩኖ አምላክ በዘመኑ የነበሩት የትግራይ፣ የአማራ እና የሸዋ የኃይማኖት እና የገዳማት መሪዎች ሰፊ ድጋፍ ነባራቸው።[19]**

**ሰለሞናውያን ከ700 ዓመተ ምህረት ጀመሮ ተዳክሞ የነበረውን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ወተዳራዊ ኃይል እጅግ እንዲንሰራራ አደረጉት። የኢትዮጵያን የግዛት ወሰንም በአስደናቂ ፍጥነት ያሰፋት ሰለሞናውያን ነግስታት ናቸው። ዳሞትን እና ጋፍትን በ1316**

---

[18] David Phillipson, *Foundations of an African Civilisation: Aksum & the northern Horn 1000 BC-AD 1300* (London: James Curry, 2012), 1-100, and 209-244; and Taddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia 1270-1527* (Oxford: The Clarendon Press, 1972), 9-68.

[19] Taddesse, *Church and State in Ethiopia,* 53-68; and Sergew Hable Sellassie, *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270* (Addis Ababa: Haile Sellasie I University, 1972), 278.

**ዓመተ ምህረት እንዲሁም በ1332 ሀድያን፣ ሰርካን፣ ደዋሮን እና ባሌን ወደ ማዕከላዊ የኢትዮጵያ መንግስት ያጠቃለሉት ጦረኛ ንጉስ የሚባሉት አጼ ዓምደ ጽዮን (1314-1344) ናቸው።[20]**

**ከዚህ ጽሁፍ ዓላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የዳሞት አውራጃ ነው። ከ1316 ዓመተ ምህረት ጀምሮ እስከ 1580 ዓመተ ምህረት ገደማ በነበረው ዘመን ዳሞት የሚገኘው በጊቤ ወንዝ እና በአዋሽ ወንዝ መካከል ባለው አካባቢ ነበር። በተጨማሪም አሁን ወለጋ የሚባለው አብዛኛው ክፍል የዳሞት አካል ነበር። አሁን ጎጃም የሚገኘው ዳሞት ከጥንቱ ዳሞት ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም። ጋፋት እና አማራ በኦሮሞ ተገፍተው የጥንት አገራችውን ሲለቁ ከፍጅት የተረፉት አብዛኛዎቹ የተሰደዱት ወደ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ እና በጌምድር ነበር። የጋፋት ዘሮች ጎጃም የሰፈሩበትን አካባቢ በጥንቱ የአገራቸው ስም ዳሞት አሉት።[21] ይህ በዓለም ታሪክ የተለመደ ነው። ለምሳሌ አውሮፓውያን አሜሪካ ሲሰፍሩ አዲሱን አገራቸውን በጥንቱ የአገራቸው ስም አዲሱ እንግሊዝ (New England)፣ አዲሱ ጀርሲ (New Jersey) እና አዲሱ ዮርክ (New York) እንዳሉት። ሩቅ ሳንሄድ ኦሮሞዎች ሲሰፍሩ የጥንቱን ተወላጆች አፈናቅለው ቦታውን በራሳቸው የጎሳ ስም ቀይረውታል። የጋፋትን ወይም የዳሞትን ታሪክ በስፋት እና በጥልቀት ያጠናችው ፈረንሳዊቷ የታሪክ ተመራማሪ አይዳ ቦውንጋ (Ayda Bounga) ናት። የዳሞትን አስደናቂ ታሪክ ማወቅ ለሚፈልግ የአይዳን ስራዎች እንዲያነብ እንጋብዛለን።[22]**

**አንባቢን እንዳያሳስት ጎጃም ያለውን ዳሞት አዲሱ ዳሞት እንለዋለን። ወለጋ እንዲሁም በጊቤ እና በአዋሽ ወንዝ መካከል የነበረውን የጥንቱን ዳሞት አሮጌው ዳሞት እንላለን። በአሮጌው ዳሞት የሚኖረው አብዛኛው ህዝብ ጋፋት እና ጉራጌ ቢሆንም አማራም ይኖር ነበር። ጋፋት ከላይ እንዳየነው የቋንቋ እና የባህል መጠሪያ ነው። ነገር ግን በ14ኛው፣ በ15ኛው እና በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመናት የተጻፉ የጽሁፍ መረጃወች ብዙ ጊዜ ጋፋትን እንደ ክፍለ ግዛት መጠሪያ ይጠቀሙበታል። አይዳ አብዛኛው ጋፋቶች ዳሞት፣ ወረብ እና እንደገብጣን በሚባሉት አውራጃዎች እንደሚኖሩ ጽፋለች (ካርታ 2ን ይመልከቱ)። እንደገብጣን በአሁኑ ምዕራብ ሸዋ በጉደር እና ሙገር ወንዞች መካከል እና የላይኛው አዋሽ አካባቢ ይገኝ ነበር። ወረብ የአሁኑ አዲስ አበባን ጨምሮ**


[20] Jules Perruchon, "Histoire des guerres d'Amda Seyon, roi d'Éthiopie," *Journal Asiatique*, Series 8, XIV (1889), 271-363 and 381-493; and Ayda Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie (XIIIe-XXe siècles): Recompositions religieuses, politiques & historiographiques (Paris, PHD dissertation submitted at the University of Paris, 2013), 11-76.

[21] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," 11-76 and 91.

[22] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie."


**ማዕከላዊውን ሸዋ እና ደቡብ ምስራቅ ሸዋን ያጠቃልላል። በዚህ ጽሁፍ ጋፋትን እንደ ግዛት ስም፣ እንደ ቋንቋ እና ባህል መጠሪያ እንጠቀምበታለን።**

**ጋፋት በጣም ሰፊ ግዛት ነበር። ባጭሩ የጋፋት መገኛ እንደሚከተለው ነው። በሰሜን የታችኛው የጃማ ወንዝ፣ በሰሜን ምዕራብ የአባይ ወንዝ እና በደቡብ የላይኛው አዋሽ ያዋስነዋል። እንዲሁም ያሁኑ ምስራቅ ወለጋ፣ ምዕራብ ሸዋ እና "ኦሮሚያ" በሚባለው ክልል ያለው ሰሜን ሸዋ ዞን ሙሉ በሙሉ በጋፋት ስር ነበር (ካርታ 3ን ይመልከቱ)።[23] የሸዋ ክፍለ ግዛት የሚያጠቃልለው አብዛኛውን በ"አማራ ክልል" ሰሜን ሸዋ የሚባለውን ሲሆን ጋፋት፣ አርጎባ እና አማራ በሰፊው ይኖሩበት ነበር። ነገር ግን በመካከለኛው ዘመን የነበረው የሸዋ ግዛት የረጋ ደንብር አልነበረውም። ብዙ የጋፋት አካባቢዎች በሸዋ ስር ነበሩ። ባጭሩ የጋፋትን፣ የዳሞትን እና የሸዋን ድንበር በገልጽ ለመለየት አዳጋች ነው፤ ህዝቡም በጣም የተቀላቀለ ነበር።[24]**




**ካርታ 2. From Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," p. 91.**

[23] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," Chapter 1-5.
[24] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," Chapter 1-5.




**ካርታ 3. Provinces of Ethiopia, Muslim territories and major trade routes in the 16th century Horn of Africa**

**የሸዋ እና የአሮጌው ዳሞት ህዝብ ታሪኩ ረጅም ቢሆንም የታሪክ መረጃ በስፋት ማግኘት የተቻለው አጼ ይኩኖ አምላክ (1270-1285) "የሰለሞናዊውን" ስርወ መንግስት "መልሰው" ባቋቋሙበት ማግስት በተለይም በ1316 አጼ አምደ ጽዮን ዳሞትን እና ጋፋትን በአስተዳደራቸው ስር ካደረጓቸው ጊዜ ጀምሮ ነው። ከ1316 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ለሁለት መቶ ተከታታይ አመታት ክርስትናን ለማስፋፋት እና ለማጠናከር የኢትዮጵያ የሃይማኖት እና የመንግስት መሪዎች የተለየ ትኩረት ከሰጧቸው አካባቢዎች ሸዋ፣ ወረብ፣ እንደገብጣን፣ አሮጌው ዳሞት እና ጉራጌ ይገኙበታል::[25] በተለይም ደግሞ በንጉሥ ዓምደ ጽዮን ዘመን የነበሩት አቡነ ያዕቆብ የተባሉት ጳጳስ የደብረ ሊባኖስ ገዳም መነኮሳትን በማሰማራት በተደራጀ መልኩ የክርስትና ኃይማኖት እንዲስፋፋ አድርገዋል። ይህ ክስተት በተለያዩ የታሪክ መረጃውች ተጽፎ ይገኛል። በአጼ ልብነ ድንግል (1508-1540) ዘመነ መንግስት የነበሩት አቃቤ ሰዓት ዮሀንስ በጻፉት ድርሳነ ዑርኤል መጽሀፋቸው ያሰፈሩት ለአብነት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፦**

> **ወበውእቱ መዋዕል ወጽአ ጳጳስ ዘስሙ ያዕቆብ ወኅረየ እምነ ውሉዱ ለአባ ተክለ ኃይማኖት ቅዱሳን መነኮሳት ፲ተወ፪ተ ወረሰዮሙ በምድረ ሺዋ ወዳሞት ከመ ሃዋርያተ ከርስቶስ ይምሐሩ ሕገ ወንጌል ተካፊሎሙ ለኅበ ፲ወ፪ቱ ክፍል ። ወዝውእቱ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ወክፍለ ፡ ሀገሮሙ ፡ፊልጶስ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወሀገረ፡ ግራርያ፡**

[25] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," Chapter 5; Taddesse Tamrat, "Ethnic Interaction and Integration In Ethiopian History: The Case of the Gafat," *Journal of Ethiopian Studies* 21 (1988), 121-154.

እስከ፡ ፈለገ ዟይ ፡ ወአኖሬዎስ ፡ ዘሀገረ ፡ ወረብ ፡ ወዘተጉለት ።ወመርቆሬዎስ ፡ ዘመርሐቤቴ ፡ ወዘመንዝሀ ፡ ወሰርማት ፡ ወማትያስ ፡ ዘፈጠጋር ወታዴዎስ ፡ ዘጽላልሽ፡ ወተስፋ ህፃን ፡ ዘብሔረ ፡ ደዋሮ ኢዮስያስ ፡ ዘወንጅ ፡ ወዘጐጐት ፡ ወዘጉራጌ ፡ ወዮሴፍ ፡ ዘሀገረ ፡ አናርዕት (እናርያ) ። መድኃኒነ ፡ እግዚእ ዘዳሞት ፡ ወስልጢ ፡ ወሳሙኤል ፡ ዘወገግ ፡ ወገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘዲቢ (ጊቤ?) ። ወእሉ ፡ አሙንቱ ፡ ተካፈልዋ ፡ ለምድረ ፡ ሸዋ ፡ ወለሀገረ ፡ ጕራጌ ፡ ለእናርዕት ወለዳሞ ት ፡ ለኅበ ፡ ፲ወ፪ቱ ከፍል ፡ ወመሐርዋ ፡ ኃይማኖተ ወንጌል ፡ ዘክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ሐዋርያት ፡ በጽድቅ ፡ በዘመነ ውእቱ ፡ ንጉሥ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮን ።

በዚያን ፡ ወራት ፡ ስሙ ያዕቆብ ፡ የተባለ ፡ ጳጳስ ወጣና ፡ ቅዱሳን ፡ መነኮሳት ከሆኑት ፡ ከአባ ፡ ተክለ ፡ ኃይማኖት ፡ ልጆች ፡ አሥራ ፡ሁለቱን ፡ መርጦ ፡ በሸዋና ፡በዳሞት ፡ ምድር ፡ ለአሥራ ፡ሁለት ፡ ክፍል ፡ ተከፋፍለው እንደ ፡ ክርስቶስ፡ ሐዋርያት የወንጌልን ፡ ሕግ ፡ እንዲያስተምሩ ፡ አደረጋቸው ። ስማቸውና ፡ ሀገረ ፡ ስብከታቸውንም ፡ እንደሚከተለው ነው ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሱና ፡የግራርያው ፡ አባ ፡ ፊልጶስ ፡የተጕለቱና ፡ የወረቡ ፡ አባ ፡አኖሬዎስ ። የመርሐ ፡ ቤቴውና ፡የመንዙ ፡ የሰርማቱ መርቆሬዎስና ፡ የፈጠጋሩ፡ ማትያስ ፡ የጽላልሹ ፡ ታዴዎስና ፡ የደዋሮው ፡ ተስፋ ፡ ሕፃን የወጁና ፡ የጎጎቱ፡ የጕራጌውም ፡ አገር ፡ ኢዮስያስና ፡የእናርዕት (እናርያ) ፡ አገር ፡ ዮሴፍ ። የዳሞቱ ፡ መድኃኒነ ፡እግዚእና ፡ የወገጐ ፡ ሳሙኤል፡የዲቢ ፡(የጊቤ?)፡ ገብረ ፡ክርስቶስ ፡ ናቸው። እነዚህም ፡ ቅዱሳን ሸዋንና ፡ ጉራጌን ፡ አናርዕትንና (እናርያን) ፡ ዳሞትን ፡ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ተካፍለው ፡ እንደ ሐዋርያት ፡ የክርስቶስን ፡ ሃይማኖትና ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ በንጉሥ። ፡ በዓምደ ፡ ጽዮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ አስተማሩ ።[26]

ከላይ ያለው ማስረጃ እንደሚያመለክተው በዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት ክርስትና በሰፊው ተሰብኳል። በዚህም ምክንያት የሸዋ ፣ የዳሞት እና የጋፋት የታሪክ ገጽታ፣ ባህል እና እምነት በጣም ተቀይሯል። በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አብዛኛው የሸዋ፣ የጋፋት እና የዳሞት አካባቢዎች ከማእከላዊ መንግስት ጋር የጠበቀ ቁርኝት ፈጠሩ። በተለይም ደግሞ በወረብ እና እንደገብጣን በተባሉት የጋፋት አገሮች ብዙ ሀብታም አድባራት ተሰርተው ነበር። ለምሳሌ ከላይ ከድርሳኑ ከተጠቀሱት 12 መነኰሳት መካከል አባ አኖሬዎስ ትውልዳቸው ጋፋት ነው። እንደገብጣን ውስጥ ሙገር ወንዝ አካባቢ ደብረ ጽጋጃ የተባለ ታላቅ ገዳም አሰርተው ነበር።[27]

ይህን ንዑስ ክፍል ከማጠቃለላችን በፊት በሰለሞናውያን ዘመን የተመዘገበውን አስደናቂ የትምህርት፣ የባህል እና የግዕዝ ቋንቋ ሥነ ጽሁፍ እድገት ባጭሩ ማቅረብ ተገቢ ነው። አጼ ይኩኖ አምላክ ከነገሱበት ከ1270 ዓመተ ምህረት ጀምሮ በ1529 ዓመተ ምህረት እስከተደረገው

[26] ድርሳነ ዑራኤል [Dersana Urael], 282-283

[27] Taddesse Tamrat, "Ethnic Interaction and Integration In Ethiopian History," 130; *idem*, *Church and State in Ethiopia*, 176; and Carlo Conti Rossini, 'Gadla Anorewos seu acta sancti Honori' (Louvain, Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium, Scriptores Aethiopici, Series Altera, 20, 1905), 1-16.

**የሽምብራ ኩሬ ጦርነት ድረስ በነበሩት 250 ተከታታይ ዓመታት የኢትዮጵያ የሥነ ጽሁፍ እና የትምህርት ወርቃማ ዘመን የሚል ስያሜ አግኝቷል። በገዳማት ትምህርት ቤቶች ብዛት እና በተጻፉት መጻሕፍት አይነትና መጠን ከዚህ ዘመን በፊትም ሆነ በኃላ ከነበረው እጅግ የላቀ ነው።[28] የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት እና ሥነ ጽሁፍ ከሰሜን እና መከካለኛው ኢትዮጵያ አልፎ እስከ ደቡብ ኢትዮጵያ የጠረፍ አውራጃዎች ተስፋፍቶ ነበር። በጋሞ አውራጃ የነበሩት ገዳማት እና ትምህርት ቤቶች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው። ጋሞ ለኢትዮጵያ መንግስት ግብር ከሚከፍሉት አውራጃዎች አንዱ እንደነበረ የመጀመሪያው የጽሁፍ ማስረጃ ለአጼ ይስሀቅ (1415-1430) በአማርኛ እና በግዕዝ የተገጠመ የወታደሮች መዝሙር ነው። በ1548 ዓመተ ምህረት አጼ ገላውዴዎስ ደዋሮ አውራጃ ልዩ ስሙ አግራሮሃ በሚባል ቦታ ክርስትያኖችን ከህገ ወጥ የባሪያ ንግድ ለመከላከል ባወጁት አዋጅ ለጋሞ እና ለዳሞት ክርስትያኖች የተለየ ትኩረት ሰጥተዋል።[29]**

**በጋሞ ከነበሩት ጥንታዊ ገዳማት እና አብያተ ክርስትያናት ውስጥ ዶይና ኪዳነ ምህረት፣ ኢሌ ገብርኤል፣ ዶሪዜ ጊዮርጊስ እና ብርብር ማርያም ተጠቃሽ ናቸው።[30] በተለይም ደግሞ የብርብር ማርያም ገዳም ታላቅ የትምህርት ማዕከል ነበር። ብርብር ማርያም ካፈራቻቸው ሊቃውንት በጣም የታወቁት በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት አባ ባህርይ ናቸው። ባህርይ በደንብ የሚታወቁት ስለ ኦሮሞ ህዝብ ታሪክ በጻፉት መጽሀፍ ቢሆንም አስደናቂ የግዕዝ ችሎታቸውን ያስመሰከሩበት ስራቸው ግን *መዝሙረ ክርስቶስ* የተሰኘው መጽሀፋቸው ነው። *መዝሙረ ክርስቶስ* የዳዊት መዝሙርን መሰረት በማድረግ የተጻፈ ነው። ይህንን በሚመለከት የመጽሀፉ አርታኢ እና አሳታሚ ጌታቸው ሀይሌ የሚከተለውን ጽፈዋል፡ "መዝሙረ ክርስቶስ በማናቸውም ረገድ መጠኑ መዝሙረ ዳዊትን ያህላል፤ እንደ መዝሙረ ዳዊት 151 መዝሙሮች አሉት። ከዚያም አልፎ፤ መዝሙሮቹ እንደ ግጥም ቤት ይመታሉ። የዳዊት መዝሙሮች በተጻፉበት**

---

[28] Christine Chaillot, *THe Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Tradition: A brief Introdcution to its Life and Spirituality* (Paris: Inter-Orthodox Dialogue, 2002), 71-100.

[29] Iganzio Guidi, "Le Canzoni Geez-Amarina in onore di re Abissini," *Rendiconti della Reale Accademia dei Lincei*, Series Quarta, V (Roma, 1889), 56; and Habtamu M. Tegegne, "The Edict of King Gälawdéwos Against the Illegal Slave Trade in Christians: Ethiopia, 1548: FEATURED SOURCE," *The Medieval Globe* Vol. 2: No. 2 (2016), 88-91. This late rsource is available at: http://scholarworks.wmich.edu/tmg/vol2/iss2/5.

[30] André Caquot, "Note sur Berber Māryām," *Annales d'Ethiopie* vol. 1 (1955), 109-116; and Jacques Bureau, 'Note sur Les Eglises du Gamo,' *Annales d'Ethiopie* vol. 10 (1976), 295-303.

**በጥንቱ በዕብራይስጥ እንጅ በትርጉማቸው ግጥሞች አይደሉም።"[31]ይህ የባህርይን የግዕዝ ችሎታ እና ብቃት ያሳያል። ምንም እንኳ የቋንቋ እውቀት እንደ ማንኛውም የእውቀት ዘርፍ በድካም እና በትምህርት የሚገኝ ቢሆንም የባህርይ የግዕዝ ችሎታ የተለየ ነው። መረጃ ባይገኝም የግዕዝ ቋንቋ ምናልባት በየገዳማቱ ይነገር ነበር ወይንም ባህርይ የተለየ የቋንቋ ችሎታ ነበራቸው። ከቤተ ክርስትያን ሊቃውንት በተጨማሪ ነገስታቱ በተለይም ደግሞ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ለግዕዝ ስነጽሁፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ንጉሱ የጻፏቸው *ጦማረ ትስብዕት* (*Epistile of Humanity*)፣ *መጽሀፈ ብርሃን* (*Book of Light*) እና *መጽሀፈ ምዕላድ* (*Book of Nativity*) የተሰኙት የህግ እና የኃይማኖት ፍልስፍና መጻህፍት ለዚህ አባባል ጥሩ ማስረጃ ናቸው።[32] ዘመኑ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍ ወርቅማ ዘመን የተባለበት ምክንያት ይህ ነው።**

**ቀጥሎ እንደምናየው በረራ የተመሰረተች በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ አባት በአጼ ዳዊት ቀዳማዊ (1380-1413) ዘመን እንደነበረ የታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ። በሌላ አነጋገር የበረራ የኢትዮጵያ ነገስታት ዋና መቀመጫ መሆን የሁለት መቶ አመታት የታሪክ የለውጥ ሂደት ውጤት ነው ወይም የመጨረሻ መደምደሚያ ነው። ከላይ በአጭሩ ያቀረብነውን የታሪክ ሂደት አይዳ ቦውንጋ፣ ታደሰ ታምራት፣ ማሪ ሎሪ ዴራት (Marie-Laure Derat) እና ስቲቨን ካፕላን (Steven Kaplan) የተባሉ የታሪክ ባለሙያዎች በሰፊው አጥንተውታል።[33] ታሪኩን በጥልቀት ለማወቅ ለሚፈልግ የነዚህን ምሁራን ስራዎች ማንበብ ይችላል። ለዚህ ጽሁፍ አላማ ግን ከላይ የቀረበው መንደርደሪያ በቂ ነው የሚል እምነት አለን።**

---

[31] Getatchew Haile, ed, *Yeabba Bahriy Dirsetoch oromochin kemmimmelekketu leloch senedoch gara* [The Works of Abba Bahriy with Other Documents concerning the Oromo] (Collegville, 1995), 36. This work is also available at: https://jontambek.files.wordpress.com/2014/03/yeabba_bahriy_dirsetoch-main.pdf.

[32] Zär'a Ya'qob, *The Epistle of Humanity of Emperor Zar'a Ya Eqob,* Corp. Script. Christ. Orient., Script. Aeth., vol. 96 (Louvain, 1991); *idem, Mäs'hafä Melad*, edited by Kurt Wendt as *Das Mashafa Milad (Liber Nativitatis) und Mashafa Sellase (Liber Trinitatis) des Kaisers Zar'a Ya'qob*, Corp. Script. Christ. Orient., Script. Aeth., vols. 41 (Louvain, 1962) and 43 (Louvain, 1963); *idem*, Zär'a Ya'qob, *Mäs'hafä Berhan,* edited and translated by Carlo Conti Rossini and Lanfranco Ricci as *Il Libro della Luce del Negus Zar'a Ya'qob (Mashafa Berhan),* Corp. Script. Christ. Orient., Script. Aeth., vol. I [vols. 47 (Louvain, 1964) and 48 (Louvain, 1965)], and Script. Aeth., vol. II [vols. 51 (Louvain, 1965) and 52 (Louvain, 1965)].

[33] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie"; Marie-Laure Derat, *Le Domaine des rois éthiopiens (1270–1527): espace, pouvoir et monachisme* (Paris: Publications de la Sorbonne, 2003); Steven Kaplan, *The Monastic Holy Man and the Christianization of Early Solomonic Ethiopia* (Wiesbaden: Coronet, 1984). Taddesse, *Church and State in Ethiopia.*

## የበረራ ታሪክ ከአጼ ዳዊት (1380-1413) እስከ አጼ ልብነ ድንግል (1508-1540)

**ስለበረራ የመጀመሪያ የታሪክ ማስረጃ በ1450 ዓመተ ምህረት የተሳለ የዓለም ካርታ ነው። በዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉስ የነበሩት አጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-1468) ናቸው። ነገር ግን የበረራ ታሪክ ከዚህ ይጀምራል ማለት አይደለም። ከተማው ተመስርቶ አድጎ ለነገስታቱ መቀመጫነት እስኪበቃ ድረስ ብዙ አመታት መፍጀቱ አይቀርም። የአፍቃል መረጃ እንደሚያስረዳው እንጦጦ (በረራ) በዋናነት የአጼ ዳዊት ከተማ እንደነበረ ነው።[34] ዳዊት የዘርዓ ያዕቆብ አባት ሲሆኑ የነገሱት ከ1380 ዓመተ ምህረት ጀምሮ እስከ 1413 ዓመተ ምህረት ነው። ስለዚህ በረራ ከፍራ ማውሮ የአለም ካርታ ላይ ከመስፈሯ በፊት ቢያንስ የአምሳ አመት እድሜ አስቆጥራለች ማለት ነው። ካርታው ወሳኝ መረጃ ስለሆነ እና ደጋግመን ስለምናነሳው ስለአሰራሩ በደንብ ማብራሪያ መስጠት ተገቢ ነው። ካርታውን በመሪነት የሳለው ፍራ ማውሮ ቬኒስ በምትባለው የጣልያን ከተማ ይኖር የነበር ሲሆን የቀድሞ ነጋዴ በኋላ የመነኮሰ እና የካርታ ስራ ባለሙያ የሆነ ነው። ፍራ ማውሮ ካርታውን የሳለው ብዙ መረጃ ከሰበሰበና ጥናት ካደረገ በኋላ በጥንቃቄ ነው። ካርታው በያዘው መረጃ ብዛትና ጥልቀት በዘመኑ ተወዳዳሪ አልነበረውም። ይህ ካርታ በብዙ መልኩ ፈር ቀዳጅ ካርታ ነው። ለምሳሌ ቀደሞ የተሰሩት የዓለም ካርታዎች ሀይማኖታዊ አስተሳሰብን የተከተሉ ናቸው። የፍራ ካርታ ግን የመጀመሪያው ሳይንሳዊ ካርታ ነው። ሳይንሳዊ የሚያደርገው ካርታው መሬት ላይ ባለው እውነታ ተመስርቶ የተሳለ እና ከሃይማኖታዊ አስተሳሰብ ይልቅ ለነባራዊ መረጃ ቅድሚያ የሚሰጥ በመሆኑ ነው።[35]**

**ካርታው 2.4 ሜትር በ2.4 ሜትር ስፋት ባለው ብራና ላይ የተሳለ ሲሆን በጣም ውድ እና ለማዘጋጀት ረጅም ጊዜ የፈጀ ካርታ ነው። ፍራ ካርታውን ያዘጋቸው በፖርቱጋል እና በቬኒስ መሪዎች ትእዛዝ ነው። ወጭውንም የሸፈኑት የኒሁ የሁለቱ አገር መሪዎች በጋራ ነው። ሁለቱም አገሮች በተለይም ፖርቱጋል አለምን በማሰስ ቀዳሚ ነበሩ። በካርታው ስራም ከፍራ በተጨማሪ ብዙ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።[36] ከላይ እንዳየነው ፍራ ለሳይንስ እድገት ላደረገው አስተዋጾ እውቅና**

[34] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped: Central Shoa on the Fra Mauro map," 12. For additional information see Gabra-Sellase, *Tarika Zaman ZaDagmawi Menilek Negusa-Nagast ZaItyoppya* (Addis Ababa: Berhanenna Sälam Printing Press, 1959 Eth. Cal.), 97.
[35] Davies, "The Wondrous East in the Renaissance Geographical Imagination," 217-222.
[36] Davies, "The Wondrous East in the Renaissance Geographical Imagination," 217-222.

**ለመስጠት በስሙ ጨረቃ አካላት ላይ ስሞች ተሰይመውለታል። የኢትዮጵያን ካርታ የሚያሳየውን ክፍል ከዚህ በታች በዋቢነት አያይዘነዋል። ፍራ ማውሮ አፍሪካን የሚመለከተውን የካርታውን ክፍል ከቦታው ተወላጆች ጠይቆ እንደሳለው የሚከተለውን ጽፏል፡-**


> **...**because to some it will appear as a novelty that I should speak of these Southern parts [of Africa], which were almost unknown to the ancients, I will reply that this entire drawing, from Sayto upwards, I have had from those who were born there. These people are clerics who, with their own hands, drew for me these provinces and cities and rivers and mountains with their names.[37]
>
> **ትርጉም**
>
> **...ምክንያቱም (በካርታው ላይ የተመለከቱትን ስለአፍሪካ) ደቡባዊ ክፍሎች ማውራቴ ለአንዳዶች አዲስ ነገር ሊሆን ስለሚችል በጥንቶችም (ባለሙያዎች) ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ስለማይታወቁ ከሰይቶ ጀምሮ ወደላይ ያለውን ጠቅላላ ስዕል ያገኘሁት ከቦታው ተወላጆች ነው ብየ እመልሳለሁ። እነርሱም ቄሶች ሲሆኑ (በካርታው ላይ ያሉትን) ክፍለ ግዛቶች፣ ከተሞች፣ ወንዞች እና ተራሮችን ከነስማቸው በእጃቸው ለኔ የሳሉልኝ እነርሱ ናቸው።[38]**

**ከዚህም በተጨማሪ ፍራ ማውሮ ኢትዮጵያን ጎብኝተው ከተመለሱ የአውሮፓ ሰዎች፣ አጼ ይስሀቅ (1414-1430) እና አጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1434-168) ወደ አውሮፓ ከላኳቸው እና ከአውሮፓ የተቀበሏቸው መልክተኞች[39] እና ከአረብ እና ከጣልያን ነጋዴዎች መረጃ የሰበሰበ ይመስላል። ቬኒስ ታዋቂ የጣሊያን የነጋዴ ከተሞች ከሚባሉት አንዷ እና ዋናዋ ነበረች። ፍራ ከመመንኮሱ በፊት ራሱ ነጋዴ ነበር። መረጃውን የሰጡት ሰዎች በተለይ የአዋሽን ወንዝ፣ በረራን እና የዝቋላን ገዳም በደምብ የሚያውቁ መሆን አለባቸው።**

**ካርታው በሚያስደንቅ ሁኔታ መሬት ላይ ያለውን እውነታ ያንጸባርቃል። በረራን በደንብ ያሳያል። የንጉሱ ዋና መቀመጫ እንደሆነም ይገልጻል። በበረራ አካባቢ የሚገኙ ከተሞችን ወንዞችን እና አድባራትን ያሳያል። ከነዚህም ውስጥ የአዋሽ ወንዝ፣ የዱከም ወንዝ፣ የዝቋላ ገዳም እና የአምባ ነገስት ተራራ ይገኙበታል። ወንዞችም ተራሮችም የዝቋላ ገዳምም ትክክለኛ ቦታቸው ላይ ተቀምጠዋል። ሁሉም እስከዛሬ ድረስ በጥንት ስማቸው ዘልቀዋል። ዱከም ከየረር ተራራ የሚመነጭ አነስተኛ ወንዝ ነው ። የዝቋላ ገዳም ላሊበላ በሚባል ወረዳ ፈጠጋር በሚባል ታላቅ የኢትዮጵያ አውራጃ ይገኝ ነበር። ፈጠጋር ከፍራ ማውሮ ከካርታው ላይ ተመልክቷል። የአዋሽ ወንዝ በመሃሉ ያልፋል (ካርታ 4ን ይመልከቱ)። ኦሮሞች የአካባቢውን ስያሜዎች ቢቀይሯቸውም ዝቋላ**

[37] Davies, "The Wondrous East in the Renaissance Geographical Imagination," 220.
[38] Davies, "The Wondrous East in the Renaissance Geographical Imagination," 217-220.
[39] Taddese, *Church and State*, 258-265

**አሁንም በጥንት ስሙ ይጠራል። ገዳምነቱም እንደ ጸና ነው። አምባነገስት የተባለው ተራራ መጠነኛ የስም ለውጥ አድርጓል። አምባነገስት የአሁኑ መናገሻ ነው። አሁንም በጫካ የተሸፈነ ቦታ ነው። እውቁ የታሪክ ባለሙያ ሪቻርድ ፓንክረስት ጫካውን ያስከበሩት አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ናቸው ይላል። መቀመጫቸውን ሸዋ ያደረጉት ሰለሞናውያን የኢትዮጵያ ነገስታት ቅባ መንግስት የሚቀቡበት መናገሻ ከተማቸው ነበር።[40]**




1 Mount Yerer
2, 3 Sets of ruins in the Yerer and Dukem groups
4 Mt. Zuqwala and summit monastery
5 Dukem/Akaki to Awash River confluence
6 Chain west of the Awash
7 Awash sources, Tefki marshes
8 Ruins of palaces on Mt Wechacha eastern slopes
9 Mt. Menaghesha, Mariam Church
10 Barara, capital city. Doors facing the pass
11 Gojjam pass
12 Entoto ridge
13 Badabedi ruins
14 Road to the east of the Entoto ridge
15 Awash river

**ካርታ 4. Map of Barara and its surrounding. The places shown on the map and others are identified by Marco. From Marco Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped,"**

**ካርታው ላይ ከሰፈሩት ስማቸው የተቀየሩ ወይም በውል ያልታወቁ ሁለት ቦታዎች አሉ። አንዱ በረራ ነው። ሌላኛው ሰደይ (ሰይ ለማለት ይመስላል) የተባለ ተራራ ነው። የሰደይን አቀማመጥ መጀመሪያ እንይ። የበረራን በኋላ እንመለስበታለን። ከዚህ በፊት የበረራን ታሪክ የተከታተለው በአዲስ አበባ እና በአካባቢ ያሉትን ጥንታዊ የቤተ መንግስት እና የቤተ ክርስቲያን ፍርስራሾች ተዘዋውሮ የጎበኘውና ጥናት ያጠናው ማርኮ ቪጋኖ (Marco Vigano) ሰደይ**

[40] Breternitz and Pankhurst, "Barara, the royal city of 15th and early 16th century (Ethiopia)," 211.

**ስለተባለው ተራራ ጥሩ ማብራሪያ ሰቷል። ይህ ጽሁፍ የተጻፍው በከፊል ማርኮ ስለቦታው ባደረገው ጥናትና ምርምር ተመስርቶ ነው። ለማርኮም ምስጋና እናቀርባለን።[41] ሰደይ ከአምባነገስት በስተምዕራብ ከእንጦጦ አምባ ሰንሰለታማ ተራሮች በስተደቡብ ከአዋሽ ወንዝ በስተ ሰሜንምስራቅ ከዝቋላ በስተ ምዕራብ ተቀምጧል። ፍራ ስለቦታው ወሳኝ የሆኑ ሁለት ተጨማሪ መረጃዎች ይሰጣል። አንደኛው እና ዋናው ሰደይ የጳጳሱ ወይም የአቡኑ መንበር ወይም መቀመጫ ነው ይላል ("Qui sta il legato e vicario del Patriarca")። ሁለተኛ ቦታው ታላላቅ አድባራት ያሉበት መሆኑን ያሳያል። ይህ ሰደይ የተባለው ተራራ ማን ሊሆን ይችላል? ሰደይ የተባለው አሁን ከአዲስ አበባ በስተ ምዕራብ የሚገኘውን የወጨጫ ተራራ ነው። ምክንያቱም ከወጨጫ ሌላ በካርታው ላይ ከተመለከተው ተራራ ጋር የሚመሳሰል አይገኝም። ማርኮ ሰደይ ከወጨጫ ውጭ ሌላ ሊሆን አይችልም ብሎ አስተያየቱን ሰጥቷል።[42]**

**ሰደይ ወጨጫ ስለመሆኑ ሁለት ተጨማሪ መረጃወች እናቀርባለን። ሁለቱም መረጃዎች ለታሪኩ ወይም ለዘመኑ እና ለቦታው ቅርበት አላቸው። አንደኛው ድርሳነ ዑራኤል ነው። ሁለተኛው የግራኝ አህመድ አድናቂ እና የግራኝን ዘመቻ ታሪክ የጻፈው የየመናዊው የአረብ ፈቂህ መጽሀፍ ነው። ከድርሳነ ዑራኤል እንጀምር። በቅድሚያ እንደጠቀስነው ይህ መጽሀፍ የተጻፈው በአጼ ልብነ ድንግል ዘመን ነው። ጸሀፊው የንጉሱ ባለሟል ከቤተ መንግስት የማይጠፉት ባለስልጣን ዓቃቤ ሰዓት ዮሀንስ ናቸው። ይህን ዓቃቤ ሰዓቱ ራሳቸው አስረግጠው እንደሚከተለው ጽፈውታል፦**

> **ወዘንተ ፡ ንባበ፡ ዘወጠነ አምዝንቱ ፡ ጽሒፎቶ ፡ ዮሐንስ ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት ፡ ዘኮነ ፡አንበሳ ፡ በፀር ፡ በዘመነ ፤ መንግሥቱ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፡ዘስመ መንግሥቱ ፡ ወናግ ሰገድ ፡ በሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሜን፡፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ሕያው ፡ ዘሀሉ ፡ አምቅድመ ፤ ዓለም ፡ ወይሄሉ ፡ እስከ ፡ለዓለም።**
>
> **ትርጉሙ**
>
> **ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይህንን መጽሐፍ ፡ መጻፍ ፡ የጀመረው ስመ ፡ መንግሥቱ ፡ ወናግ ሰገድ፡ ወይም ፡ አንበሳ ፡ በፀር፡በተባለው ፡በኢትዮጵያዊው ፡ንጉሥ ፡ በልብነ፡ ድንግል ፡ዘመነ ፡ መንግሥት ፡በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ዮሐንስ፡ ዓቃቤ ፡ ሰዓት፡ ነው ፡፡አሜን ፡፡ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ፡ ወደፊትም ፡ ለዘላዓለም ፡ የሚኖር ፡ ሕያው ፡በሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡አብ ፡ ስም።"[43]**

[41] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped Central Shoa on the Fra Mauro map, 5-8.
[42] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped Central Shoa on the Fra Mauro map, 6.
[43] ድርሳነ ዑርኤል [Dersana Urael], 318-319.

**መጽሀፉ ዑራኤል የተባለው መልአክ የኢትዮጵያን አድባራትና ገዳማት እየተዘዋወረ እንዴት እንደባረካቸው ያትታል። መልአኩ የሰራቸው ታምራት ለታሪክ መረጃነት አይጠቅሙም። ከተአምሩ ውጭ የሰፈረው አብዛኛው የመጽሀፉ ይዘት ግን ታማኝ እና ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ ታላላቅ መነኮሳት እና ነገስታቱ የመሰረቷቸውን አድባራት፣ የሚገኙበት ቦታ እና የተመሰረቱበትን ዘመን ድርሳኑ ይዘረዝራል። ሁሉንም ባይሆንም አብዛኛዎችን አድባራት በገለልተኛ ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ደብረ ሰይ ይባላል። ደብረ ሰይ የተባለው ቤተክርስትያን ፍራ ማውሮ ካርታ ላይ ሰደይ ከተባለው ጋር በስም ይመሳሰላል። ምናልባት ፍራ መረጃውን ካርታው ላይ ሲጽፍ የቃላት ግድፈት ወይም ስህተት አድርጎ ሰይን ሰደይ ብሎት ይሆናል። ካርታው በእጅ ስለተሰራ እንዲህ አይነቱ ጥቃቅን የፊደል ግድፈት የተጠበቀ ነው። ይህ አዲስ መረጃና የበረራንም አቀማመጥ በእርግጠኝነት ለመናገር ስለሚረዳ ዓቃቤ ሰዓት ዮሀንስ ድርሳኑ ላይ ያሰፈሩትን በዝርዝር ማቅረብ ተገቢ ነው። ዝርዝሩ የሚቀጥለው ነው፡-**

**ወሐነጸ ፡ ናዖድ ፡ ንጉሥ፡ ዓቢየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዲበ ፡ ሀገረ ፡ በዬ (ዮ)፡ ኀበ ፡ ከተማሁ ፡ ለውእቱ መኰንን ፡ ዘተብህለ ፡ ሰይ ፡ራስ ፡ በስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ማርያም፡ ድንግል ፡ወላዲት ፡ አምላክ ፡ ወሰመያ ፡ደብረ ፡ ሰይ ።ወሠርዓ ፡ በውስቴታ ፡፫ተወ፬ተ ፡ ፲ተወ፳ተ ፡ ከህናተቅዱሳነ ፡ ለዝማሬሃ ፡ ወለቅዳሴ ፡ቊርባን ። ፯ ፲ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ኢይፃአ ፡ መንበረ ፡ ጳጳሳት ፡ እመንበ ረ ፡ ክብ ራ ። ወኢይግበ ሩ ፡ ተድባበ ፡ ርእሶሙ ፡ ንቡራነ ፡እድ ፡ ዘሀገረ ፡ መሐግል ፡ወጳጳስ ፡ ወመምህር ፡ ዘደብረ ሊባኖስ ፡ አመ ፡ መጽኡ። ፡ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ደብር ። ወእሉ ፡ ንቡራነ ፡ እድ ይግበሩ ፡ ተድባበ ፡ ምስለ ፡ጳጳስ ፡ መትሐቲሁ ፡ ለጳጳስ ። እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ገቢሮት ፡ በውስቴታ ፡ ተድባበ ፡ ዘእንበለ ፡ ይእቲ ፡ በዓለ ፡መንበር ። አስመ ፡ ተቀብረ ፡በውስቴታ ፡ ክቡር ፡ ጳጳስ ፡አባ ፡ ማርቆስ ፡ ዘአፍለሰ ፡ዓጽመ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖ ት ፡ በከብር ። ወንቡረ ፡ አድ ፡ ዘደብረ ፡ ሊባኖለ ፡ ገቢሮቱ ፡ትድባበ ፡ በእንተ ፡ ገቢዖቱ ፡ቀዳሚ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ አም አኅጉራተ ፡ ክተታ ፡ ቀዲሙ። አምዝኒ ፡ ገብረ ፡ ቤተክርስተያን ፡ በስመ ፡ ቅዱስ ፡ዑራኤል ቀዳሚ። ወሥልሰ ፡ ገቢሮቱ ፡ተድባበ ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ ዘሀገረ ፡ መሐግል ፡ ስብከተ ፡ዕፃሁ ፡ ለቀውስጦስ ፡ ንቡረ፡ እድ ፡፡፡ ወአሐዱ ፡ ስሙ ፡ ለቀውስጦስ ፡ አቡነ ፡ ዳዊት ፡በእንተዘኮነ ፡ ሰማዕተ ፡በይነ ፡ ተጋድሎቱ ፡ በኃይማኖት ፡ ርትዕት ፣ ከርስቶሳዊት ፡ ምስለ ፡ ዕልዋን ፡ ነገሥት ። ወአክበራ ፡ ለይእቲ ፡ ደብር፡ ናዖድ ፡ ንጉሥ ፡ አምደብረ ፡ ዓባይ ፡ ወአክሱም ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ፡ ወሀቦ ፡ ለናዖድ ፡ እግዚእነ ፡ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ኪዳነ ምሕረት ፡ ከመ ፡ ኢይጥፋእ ምስፍና ፡ ወምልክና ፡ በምድረ ሸዋ ፡ ወመንዝህ ወበሀገረ ፡ ጐራጌ ፡ ዘይብልዎ ምድረ ፡ ወረብ ፡ ወምሁር።**

**ትርጉም**

**ንጉሥ ናዖድ ፡ ራስ ፡ሰይ ፡ በተባለ ፡ በዚሁ ፡ መኰንን ፡ ከተማ ፡ በዬ (ዮ)፡ ውስጥ አምላከን ፡ በወለደች ፡ በእመቤታችን ድንግል ፡ ማርያም ፡ ስም ፡ታላቅ ቤተ ፡ክርስተያን ፡ ሠራና ፡ ስሟንም ፡ ደብረ ፡ ሰይ ፡ አላት ። በውስጧ መስዋዕትን የሚሠዉና ፡ በማኅሌት የሚዘምሩ ፡ ቅዱሳን ፡ የሆኑ፡ ሶስት ፡ መቶ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ካህናትን ፡ አዘጋጀ ፡ወይም ፡ ተከለ ። መንበረ ፡ ጳጳሳቱም ፡ከዚችው ፡ ደብር ፡ ወደ ሌላ ፡እንዳይዛወር ፡ ወይም**

: አንዳይወጣ ፡ አዘዘ ። የመሐግል ፡ ሀገር ፡ንቡራነ ፡ እድና ፡ ጳጳስ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስም ፡ መምህር ፡ወደዚች ፡ ደብር ፡ በመጡጊዜ ፡ ለራሳቸው ፡ ድባብን ፡አያድርጉ ፡ ሲል ፡ አዘዘ ። ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አነዚህ ንቡራነ ፡ አዶች ፡ ከጳጳሱ ፡በታች ፡ በመሆን ፡ ከጳጳሱጋር ፡ ድባብን ፡ ያሲዙ ። በዚችው ፡ ደብር ፡ውለጥ ፡ ድባብን ፡ ማድረግ ፡ ያለደብሯ፡ መንበረ ፡ጳጳስ ፡ በቀር ፡ ክልክል ፡ነው ። ዳግመኛም ፡ የአባታችን ፡ የአቡነ ፡ ተክለ ፡ ኃይማኖትን ፡ ዓፅም ፡ ያፈለሰ ፡ ክቡር የሆነ ፡ ጳጳስ ፡ አባ ፡ ማርቆስ ፡በውስጧ  ተቀብሯልና ። የደብረ ፡ ሊባኖሱ ፡ንቡረ ፡ እድም ፡ ድባብ ፡ ማድረጉ ፡ ከከተታ ፡ አገሮች ፡ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ በመግባቱ ነው ከዚህም ፡ በላይ ፡በመጀመሪያ ፡ በቅዱስ ፡ዑራኤል ፡ ስም ፡ ቤተ ክርስትያን ፡ ሠርቷልና ። ሶስተኛም ፡ የመሐገሉ ፡ ሀገር ፡ ንቡረ ፡ እድ ፡ድባብ ፡ የሚያደርገው ፡ ንቡረ እድ ፡ የሆነው ፡ የቀውስጦስ፡የስብከቱ ፡ ክፍል ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። የቀውስጦስም ፡ አንደኛው ፡ስሙ  አቡነ ፡ ዳዊት ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡ ከካሀዲዎች ፡ ወይም ፡ ከአላውያን ፡ነገሥታት ፡ ጋር ፡ የክርስቶስ ፡እምነት ፡ በሆነች ፡ በቀናች ኃይማኖት ፡ ተጋድሎ  አድርጎ ፡ ሰማዕት ፡ ስለሆነ፡ ነው ። ይህችንም ፡ ደብር ንጉሥ፡ ናዖድ ከደብረ ዓባይና ፡ ከአክሱም ፡ አብልጦ ፡ አከበራት ። ከዚሀ ፡ በኋላ ፡ ጌታ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ከምድረ ፡ ሸዋ ፡ ምሁርና ፡ምድረ ፡ ወረብ ፡ ከሚባለው ከጉራጌ ፡ አገር ፡ ከመንዝም ፡አገዛዝና ፡ መስፍንነት ፡ አንዳይጠፋ ፡ ለናዖድ ፡ ቃል ፡ኪዳን ፡ ሰጠው።[44]

ከላይ የቀረበው ጥቅስ አብዛኛው ግልጽ ስለሆነ ተጨማሪ ማብራሪያ አያስፈልገውም። ዓቃቤ ሰዓት ዮሀንስ ስለ ደብረ ሰይ ሶስት ወሳኝ መረጃ አስፍረዋል። አንደኛው ቤተ ክርስቲያኑ ትልቅ መሆኑን እና መስራቹ አጼ ናዖድ መሆናቸውን። ሁለተኛ ደብረ ሰይ የጳጳሳቱ መንበር መሆኑን፣ ለጳጳሱ በሚገባ ክብር ደብረ ሰይ የኢትዮጵያ ርዕሰ አድባር እንደሆነች ጨምሮ ይገልጻሉ። ሶስተኛ አቡነ ማርቆስ የተባሉ ጳጳስ በደብረ ሰይ እንደተቀበሩ ድርሳኑ ይገልጻል። በመጨረሻም መላኩ ዑራኤል ለአጼ ናዖድ ገዢነት ወይም መሥፍንነት ከወረብ፣ ከመንዝና ከጉራጌ እንዳይወጣ ቃል ኪዳን እንደሰጣቸው ይናገራል። ይህ ነገስታቱ ከሸዋ፣ ከወረብ እና ከጉራጌ ጋር ያላቸውን ቅርበት ያሳያል። ከላይ በረራ በወረብ ወስጥ እንደሚገኝ ተናግረናል። አጼ ናዖድ ያሰሩት የደብረ ሰይን ቤተክርሲቲያን ብቻ አይደለም። አማራ ሳይንት ውስጥም መካነ ሥላሴ የሚባለውን ታላቅ ቤተክርስትያን እንዳሰሩ ይታወቃል። ይህ ቤተ ክርስትያን በግራኝ ሰራዊት ከተዘረፈ በኃላ ተቃጥሏል።[45] ከድርሳነ ዑራኤል ሌላ ስለ ደብረ ሰይ ተጨማሪ የሀገር ውስጥ የታሪክ መረጃ የለም፡ ፡ ከውጭ አገር ጸሀፊዎች ግን አረብ ፈቂህ ከበረራ ከተማ በቅርብ ርቀተ የሚገኝ አጼ ናዖድ ያሰሩት ቤተ ክርስትያን እንደነበረና የግራኝ ወታደሮች እንዳቃጠሉት ጽፏል። ዝርዝሩ ከዚህ በታች ቀርቧል።

[44] ድርሳነ ዑርኤል [Dersana Urael], 311-315.

[45] Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia*, 246-247.

**አረብ ፈቂህ በረራ የሚገኘው የአጼ ልብነ ድንግል ቤተ መንግስት በግራኝ ሰራዊት ከተዘረፈ በኋላ እንደተቃጠለ ጽፏል። ይህ የሆነው በ1530 ዓመተ ምህረት ነው። በዚሁ ዓመት ግራኝ ለ6 ቀናት በረራ ላይ ተቀምጦ ዘራፊዎችንና ቤተ ክርስትያን የሚያቃጥሉ በአቅራቢያው ባሉ ቦታዎች ያሰማራ ነበር።በዚህ መሰረት ጋረድ ጃሽዋ (**Garad Jausah**) የሚባል የግራኝ ታማኝ ከበረራ በቅርብ እርቀት ወደ ሚገኝ ቦታ ተልኮ በጣም ብዙ ወርቅ እና ብር እንዲሁም ከሀር የተሰራ ብዙ አልባሳት ዘርፎ እንደተመለሰ አረብ ፈቂህ በሰፊው ያትታል። የተዘረፈውን ቤተ ክርስትያን በጣም ታላቅ ሲል ይገልጸዋል። ቤተ ክርስትያኑን ያሰሩት ደግም አጼ ናዖድ ናቸው ይላል። የተቃጠለው ቤተ ክርስትያን የሚገኘው የጳጳሳቱ መቀመጫ በሆነ ቦታ እንደሆነ አረብ ፈቂህ ጨምሮ ጽፏል። በመጨረሻም ቤተ ክርስትያኑ ውስጥ አጽሙ በሳጥን በክብር የተቀመጠ የቀድሞ ጳጳስ አብሮ እንደነደደ በዝርዝር ተቀምጧል።[46] አረብ ፈቂህ የቦታውን ስም ባይናገረም ተዘርፎ የተቃጠለው የአጼ ናዖድ ቤተ ክርስቲያን ድርሳነ ዑርኤሉ ላይ አጼው አሰሩት ከተባለው ቤተ ክርስትያን ጋር ፍጹም ተመሳሳይ ነው። ሥለዚህ ፍራ ማውሮ ከሳለው የአለም ካርታ ላይ የተመለከተው ሰደይ የተባለው የጳጳሳቱ መቀመጫ ቦታ፣ በረራ አቅራቢያ የግራኝ ወታደሮች ዘርፈው ያቃጠሉት የአጼ ናዖድ ቤተ ክርስትያን እንዲሁም ድርሳነ ዑራኤል ላይ የተጠቀሰው አጼ ናዖድ ያሰሩት ደብረ ሰይ የተባለው የጳጳሳቱ መቀመጫ ቤተ ክርስትያን ሁሉም ተመሳሳይ ናቸው። ከነዚህ ጠቃሚ መረጃዎች በመነሳት የጳጳሳቱ መቀመጫ ከመናገሻ በስተ ምዕራብ የሚገኘው አሁን ወጨጫ የሚባለው ተራራ ነው በማለት መደምደሚያ መስጠት ይቻላል። ይህም የበረራን ትክክለኛ ቦታ ለማወቅ ትልቁን ድርሻ ይይዛል።**

**የፍራ ማውሮን ካርታን ጨምሮ ስለበረራ ብዙ መረጃ ተገኝቷል። በረራ ከዱከም ወንዝ በስተምዕራብ፣ ከአዋሽ ወንዝ በስተሰሜን እና ከአምባነገስት በስተምስራቅ እንደሚገኝ የፍራ ማውሮ ካርታ ያሳያል (ካርታ 4ን ይመልከቱ)። አረብ ፈቂህ በረራን ከአስር ጊዜ በላይ በስም ጠቅሷታል።[47] በተጨማሪም አሌሳንድሮ ዞርዚ ሰለ በረራ የሰበሰበው መረጃ በጣም ጠቃሚ ነው። ዞርዚ በጣሊያኗ ከተማ በቬኒስ ይኖር የነበር የታሪክ ተመራማሪ እና የካርታ ስራ ባለሙያ ነው። መረጃውን የሰበሰበው ከ1470 እስከ 1523 ባሉት ዓምሳ አምስት አመታት ሲሆን የመረጃ ምንጮች ደግሞ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ የተመለሰ በስም ያልተጠቀሰ ቬኒሳዊ፣ ፍራንቸስኮ ሱሪአኖ ከሚባል ጣሊያናዊ ተጓዥ እንዲሁም ጣሊያን በስደት ይኖሩ ከነበሩት ዞርጊ፣ ሩፋኤል፣ ቶማስ እና እንጦንዮስ**

[46] Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia*, 166-167.
[47] Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia*, 165-224.

**ከሚባሉ የኢትዮጵያ መነኮሳት ነው።[48] ዞሪዚ ስለ በረራ የሰበሰባቸውን መረጃዎች እንግሊዛዊው የታሪክ ተመራማሪ እና የቅርስ ጥበቃ እና እንክብካቤ ባለሙያ ክራውፎርድ የኢትዮጵያ የጉዞ ማስታወሻዎች (***Ethiopian Itineraries ca. 1400-1524)*** በሚል ርዕስ ተርጉሞ አሳትሟቸዋል። ክራውፎርድ የበረራን ታሪክ እና መገኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የጻፈ ፈር ቀዳጅ ተመራማሪ ነው። በዚህም ሊመሰገን ይገባዋል።[49]**

**የጣሊያኖችም የኢትዮጵያ መነኮሳትም በረራ የኢትዮጵያ መዲና እንደሆነ ይናገራሉ። የኢትዮጵያ መነኮሳት ወደ ጣሊያን የተሰደዱበት ምክንያት የኦቶማን ቱርክ ወታደሮች በ1517 ዓመተ ምህረት እየሩሳሌምን በኃይል በያዙበት ወቅት የኢትዮጵያ ገዳማት ሰለተደመሰሱ ነው። በአውሮፓ የመነኮሰ፤ ቆብ የደፋ ወንድም መባል የተለመደ ስለነበር ዞርዚ ወንድም እያለ ይጠራቸዋል። እኛ ግን በኢትዮጵያ ልማድ አባ እያልን እንጠራቸዋለን። አባ ዞርጊ፣ አባ ሩፋኤል፣ አባ ቶማስ እና አባ እንጦንዮስ ለምናኔ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ በረራን አቋርጠው ነው የሄዱት። የብዙዎቹ የትውልድ አገራቸው የያኔው ደቡብ ኢትዮጵያ ነበር። አባ እንጦንዮስ የአርጌው ዳሞት ተወላጅ ሲሆኑ ቶማስ ደግሞ ተወልደው ያደጉት በረራ ነው። ዞርጊ የወጅ አውራጃ ተወላጅ ናቸው። ወጅ በዝዋይ ሀይቅ ዙሪያ ያለ ታላቅ የኢትዮጵያ አውራጃ ነበር (ካርታ 1ን ይመልከቱ)። አማራ፣ ጉራጌ እና የዛይ ቋንቋ ተናጋሪዎች በስፋት ይኖሩበት ነበር። አጼ በዕደ ማርያም (1468-1478) እና አጼ ገላወዴዎስ (1540-1559) ወጅ ውስጥ ቤተ መንግስት ነበራቸው። ለዚህ ሁሉ ማስረጃ በአጼዎቹ ዘመን የተጻፉ ዜና መዋዕሎች ናቸው።[50] ከላይ ድርሳነ ዑርኤልን እንዳየነው ክርስትናም በጣም ተስፋፍቶበት ነበር። የአባ ሩፋኤልን የትውልድ ቦታ ማወቅ አልተቻለም።**

**አባ ዞርጊ በረራ ወረብ ከሚባለው አውራጃ እንደሚገኝ እና የንጉሱም የጳጳሱም መቀመጫ እንደነበረ ያረጋግጣሉ። ዞርጊ ከበረራ ተነስተው በደብረ ብርሃን አድርገው ነው ወደ ኢየሩሳሌም የሄዱት። ከበረራ ደብረ ብርሃን ቀጥታ ስላልሄዱ ጉዞውን ለመጨረስ የፈጀባቸውን ጊዜ ለማወቅ አልተቻለም። በረራ የአባ ሩፋኤል የጉዞ መነሻ ቢሆንም የተጓዙበት አቅጣጫ ግልጽ አይደለም። ከሁሉም መነኮሳት ይልቅ አባቶማስ የሰጡት መረጃ የበረራን አቀማመጥ ለመረዳት ያስችላል። አባ**

[48] Breternitz and Pankhurst, "Barara, the royal city of 15th and early 16th century (Ethiopia)," 213-214
[49] Crawford, *Ethiopian Itineraries ca. 1400-1524,* 41-193.
[50] William Conzelman, *Chronique de Galâwdêwos (Claudius) Roi d'Éthiopie, Texte Éthiopien traduit, annoté et précédé d'une Introduction Historique* (Paris, 1895), 33; and Jules Perruchon, *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et de Ba'eda Mâryâm, Rois d'Éthiopie de 1434 à 1478 (Texte Éthiopien et Traduction), Précédées d'une Introduction* (Paris: Émile Bouillon, 1893), 180.

**ቶማስ በረራ በወረብ እንደሚገኝ ፣ የነገስታቱ መቀመጫ እንደሆነ ቤተ መንግስቱም ከተራራ ላይ እንደሚገኝ እና በረራን ጨምሮ ወረብ ለኑሮ ተስማሚ ወይና ደጋማ የአየር ንብረት እንዳለው ይናገራሉ። ይህ መረጃ በረራን ከእንጦጦ ጋር ያመሳስላል። አባ ቶማስ ጉዟቸውን የጀመሩት ከወጅ ነው። ከወጅ ተነስተው በረራ ለመድረስ 6 ቀን ፈጀብኝ ይላሉ። በተጨማሪም የአዋሽ ወንዝ ከሚመነጭበት ከጋፋት ተራራ ተነስቶ በረራ ለመድረስ 20 ቀን እንዲሁም ከዳሞት እስከ በረራ 15 ቀን የእግር ጉዞ እንደሚፈጅ ለአሌሳንድሮ ዞርዚ ተናግርዋል። በመጨረሻም ንጉሱ የእጅ ጥበብ ባለሙያዎችን በበረራ እና በሌሎችም ከተሞች እንደሚያሰፍር ይናገራሉ።[51] ከላይ የተቀመጠው መረጃ በረራን ከደብረ ብርሃን በስተ ደቡብ በቅርብ እርቀት እንደምትገኝ ለማወቅ ያስችላል። ቀጥሎ እንደምናየው ተመሳሳይ መረጃ አረብ ፊቂህ መጽሀፍ ላይ ሰፍሯል።**

**ግራኝ በ1529 ዓመተ ምህረት ከአሁኑ ደብረ ዘይት አካባቢ በሚገኝ ሽምብራ ኩሬ በተባለ ልዩ ቦታ ላይ በተደረገው የአንድ ቀን ጦርነት በቁጥር የሚበልጠውን የአጼ ልብነ ድንግልን ሰራዊት አከርካሪውን ለመስበር ችሏል። አረብ ፈቂህ የግራኝን ሰራዊት እግር በግር እየተከታተለ የጦርነቱን ሂደት እና በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን ውድመት በአይኑ የተመለከተውን እና ሰዎችን እየጠየቀ ያገኘውን በስፋት ዘግቦታል። አረብ ፈቂህ ግራኝንና ሰራዊቱን ያደንቃል፤ ያሞግሳል እንዲሁም ሲዋጉ የሞቱትን እግዚአብሄር ነፍሳቸውን በገነት እንዲያኖር ይለምናል። በተቃራኒው የልብነ ድንግልን ወታደሮች እና መኮንኖች ባጠቃላይ ክርስቲያኖችን በያንዳንዱ የመጽሃፉ አንቀጽ የስድብ እና የእርግማን ውርጅብኝ ያወርድባቸዋል። የመጽሀፉ ረቂቅ የተጻፈ በጦርነት ጊዜ ስለሆነ ስድብ እና እርግማን ሊኖረው እንደሚችል የሚጠበቅ ነው። የአረብ ፍቂህ መጽሀፉ በታሪክ ባለሙያዎች በጣም ታማኝነት ያለው መጽሃፍ ነው። አንዳንድ ቦታ ላይ የሚያደናግር ነገር ቢጽፍም አረብ ፍቂህ ስለ ኢትዮጵያ መልካ ምድራዊ አቀማመጥ ጠቃሚ መረጃ አስፍሯል። አብዛኛዎችን ቦታዎች፣ ቤተክርስትያኖች፣ የነገስታቱን እና የመኳንቶችን ስምና ታሪክ እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ምንም ሳያምታታ ጽፎታል። የመናዊ ይሁን እንጅ አረብ ፈቂህ ኢትዮጵያን በደንብ የሚያውቅ ስለመሆኑ የጻፈው መጽሀፍ ይመሰክራል። አረብ ፈቂህ ሰለ በረራ ብዙ የሚለው አለው።[52]**

[51] Crawford, *Ethiopian Itineraries ca. 1400-1524,* 64-193.

[52] See the view of the English language editor and translator of the work under the "Introdcution" in Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia,* vii-xxiii.

ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ከአንድ አመት በኋላ የግራኝ አውዳሚ ዘመቻ ያነጣጠረው በወረብ አውራጃ ነበር። ወረብ ሰፊ፣ ለምና በጣም ሀብታም አውራጃ ነበረ። አረብ ፈቂህ የሃበሾች ምድራዊ ገነት ይለዋል። ተወላጆች አማሮች፣ ጋፋቶች እና ጉራጌዎች ነበሩ። በረራ እና ሁለተኛው የንጉሱ ቤተ መንግስት የሚገኝበት ባደቄ የተባለው ከተማም የሚገኙት ከዚሁ ከወረብ አውራጃ ነበር። ባደቄ ከበረራ በጣም በቅርብ እርቀት የሚገኝ ከተማ ነው። የፍራ ማውሮ ካርታ ግን ባደቄን ዘሎታል። አረብ ፈቂህ ትውልዷ ትግሬ የሆነች የንጉሱ እናት ያሰራችው ታላቅ ቤተ ክርስትያን በባደቄ እንደሚገኝ ጽፏል። ከትግራይ የመጡ የንጉሱ ዘመዶች ቤተ ክርስትያኗን አንዳትቃጠል በቆራጥነት እንደተዋጉ የግራኝንም ወታደሮች ለጊዜውም ቢሆን እንዳሸነፏቸው ጽፏል። ስለ ንጉሱ እናት የተሰጠው መረጃ ትክክል ሊሆን ይችላል። በሽምብራ ኩሬ ጦርነትም ካለቁት የልብነ ድንግል ታላላቅ መኮንኖች ትግሬዎች ይገኙበታል።[53] ምናልባትም የንጉሱ የቅርብ ዘመዶች ሊሆኑ ይችላሉ።

በ1530 ዓመተ ምህረት ግራኝ ከአዋሽ ወንዝ ምንጭ ጀምሮ እስክ በረራ ለመድረስ 10 ቀን እንደፈጀበት አረብ ፈቂህ ይጽፋል። ይህ ግን ትክክል አይመስልም። ከላይ እንዳየነው አባ ቶማስ ከአዋሽ ወንዝ ምንጭ ተነስተው በረራ ለመድረስ 20 ቀን እንደፈጀባቸው ለዞርዚ ነግረውታል። ስለዚህ የግራኝ መነሻ ነጥብ የአዋሽ ምንጭ ሊሆን አይችልም። እራሱ አረብ ፈቂህ እንዳየው የግራኝ ወታደሮች በየመንገዱ ያገኙትን እየዘረፉ እና እያቃጠሉ ስለሚሄዱ ጉዟቸው በጣም ዘገምተኛ መሆን አለበት።[54] ስለዚህ ከአዋሽ ወንዝ ምንጭ ከጋፋት ተራራ (የዛሬው ጊንጪ አካባቢ) ተነስተው በየመንገዱ እየዘረፉ፣ ቤተ ክርስትያን እያቃጠሉ በረራ በ10 ቀን ሊደርሱ አይችሉም።

አረብ ፈቂህ ከግራኝ ሰራዊት ጋር በረራ ከደረሰ በኋላ ያየውን ጽፏል። በንጉሱ ስር የሚተዳደሩ የእጅ ባለሙያዎች በረራ ከተማ እንደሚኖሩ ጽፏል። እነዚህ የእጅ በለሙያዎች ለንጉሱ እና ለቤተ መንግስት ሰራተኞች ልብስ የሚሰፉ ለንጉሱ ፈረሰኛ ወታዶሮች ፈረሶችን ከጦር የሚከላከል የብረት ጥሩር የሚሰሩ እንደነበሩ ይናገራል። ግራኝ በረራን ሲይዝ ባለሙያዎች ከአጼ ልብነ ድንግል ጋር በፈጠጋር አውራጃ አብረው እንደነበሩ፤ ንጉሱ ሸሽተው ወደ ወጂ ሲሄዱ ባለሙያዎች ወደ በረራ እንደተመለሱ እና ለሙስሊሞች አቀባበል እንዳደረጉላቸው አረብ ፈቂህ ጨምሮ ጽፏል። ግራኝ በረራ ተቀምጦ ሳለ ደብረ ሊባኖስ ከበረራ ምንያህል እርቀት እንዳለው ጠይቆ ነበር። አረብ ፈቂህ ከበረራ ደብረ ሊባኖስ የ6 ቀን የእግር ጉዞ እንደሆነ የበረራ ሰዎች ለግራኝ

[53] Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia,* 62-87, 165-224.
[54] Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia,* 185.

**እንደነገሩት እና ግራኝም ድል ሰገድ እና ቀጭን አቡ በከር የሚባሉ ታማኞቹን ከ300 ወታደሮች ጋር ገዳሙን ዘርፈው እንዲያቃጥሉት ትዛዝ ሰጥቶ እንደላካቸው እና በትዛዙም መሰረት ደብረ ሊባኖስ ተዘርፎ እንደተቃጠለ ያትታል።[55] ይህ በረራ ያለበትን ቦታ ለማወቅ ያስቻለ ተጨማሪ ወሳኝ መረጃ ነው። ከታች እንደምናየው በአረብ ፈቂህ መረጃ መሰረት ከአዲስ አበባ እስከ ደብረ ሊባኖስ ያለው ረቀት የ6 ቀን የእግር ጉዞ እንደ ሆነ ስለ በረራ ጥናት ያደረገ እንድ የወጭ አገር ተመራማሪ እራሱ በእግሩ ተጉዞ አረጋግጧል።**


**ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃወች መሰረት በማድረግ የታሪክ ተመራማሪዎች ሥለበረራ ትክክለኛ ቦታ የተለያየ መላምት ሰጥተዋል። ለምሳሌ ሀርትዊግ ብሬተርኒዝ እና ክራውፎርድ የበረራ ትክክለኛ መገኛ ዱከም ወንዝ የሚመነጨበት የረር ተራራ አካባቢ ነው ይላሉ (ካርታ 5ን ይመልከቱ) ። በመረጃነት የተጠቀሙት ደግሞ አረብ ፈቂህንና የረር ወስጥ ልዩ ስሙ እንስላል የተባለ ቦታ የተገኘ የግንብ ፍርስራሽ ነው።[56] ሆኖም ድምዳሜያቸው ከሌሎች መረጃዎች ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ተቀባይነት አይኖረዉም። ለምሳሌ ከፍራ ማውሮ ካርታ ጋር አይገጣጠምም። በረራ የረር ነበር ከተባለ ከዝቋላ ገዳም ጋር በጣም ይቀራረባል። ይህ ማለት ደግሞ በረራ እንደ ዝቋላ ገዳም በፈጠጋር አውራጃ ወስጥ ነበር ማለት ነው። ከላይ እንዳየነው አረብ ፈቂም ሆነ የኢትዮጵያ መነኮሳት በረራ በወረብ አውራጃ እንዳለ መስክረዋል። ማርኮ ቪጋኖ እና ብሩስ ስትራካን (Bruce Strachan) በበኩላቸው በረራ የሚገኘው በሰሜን አዲስ አበባ በተለይም እንጦጦ ራጉኤል አካባቢ እንደሆነ አረጋግጠዋል። ባጭሩ የበረራና የባደቂ መገኛ ያሁኑ አዲስ አበባ ነው ወደሚል ድምዳሜ ደርሰዋል። ብሩስ ከደብረ ሊባኖስ ጀምሮ አዲስ አበባ ድረስ በእግሩ ተጉዞ ሰሜን አዲስ አበባ ለመድረስ 6 ቀን እንደፈጀበት እና የአረብ ፈቂህ መረጃ ትክክል እንደሆነ አረጋግጧል። በረራ የአሁኑ አዲስ አበባ ነው ለማለት ያስቻለው ይህ ነው።[57]**

---

[55] Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia,* 186-187 and 192. እነ ድል ሰገድ ደብረ ሊባኖስን ዘርፈው ካቃጠሉ በኋላ በራራ ለመመለስ 12 ቀን ፈጅቶባቸዋል።አስራ ሁለት ቀን ደርሶ መልስ ይሁን አይሁን አራብ ፈቂህ በግልጽ አላስቀመጠውም።

[56] Crawford, *Ethiopian Itineraries ca. 1400-1524,* 195-196; and Breternitz and Pankhurst, "Barara, the royal city of 15th and early 16th century (Ethiopia)," 228.

[57] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped," 5-14; and Bruce Strachan, "Barara: Abyssinia's Lost Mediveal City" (https://cityofbarara.wordpress.com/ accessed on July 31, 2017).




**ካርታ 5. From Breternitz and Pankhurst, "Barara, the royal city of 15th and early 16th century (Ethiopia)," 231.**

**ማርኮ ቪጋኖ በሳተላይት ምስል (satellite imaging) በመታገዝ የፍራ ማውሮን ካርታ በአዲስ መልክ እና በጥልቀት አጥንቶታል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ ዙሪያ የተገኙትን የቤተመንግስት እና የቤተክርስትያን ፍርስራሾችን ተዘዋውሮ ጥናት አድርጓል፤ በመረጃነትም ተጠቅሟል። ሁሉም መረጃዎች የሚጠቁሙት ይላል ማርኮ ቪጋኖ የጥንቱ በረራ የአሁኑ አዲስ አበባ እንደሆነ ነው። ማርኮ እንደሚለው ከሆነ ፍራ ማውሮ ካርታ ላይ የዱከም ወንዝ ተብሎ የተጠቀሰው በስተት የአቃቂን ወንዝ ነው። ሀርትዊግ ብሬተርኒዝም በበኩሉ ካርታው ላይ የተመለከተው ወንዝ የአቃቂ ወንዝ መሆን አለበት ይላል። ለዚህ ድምዳሜ እንደ ምክንያት የቀረበው በካርታው ላይ የተመለከተው ወንዝ የፍሰት አቅጣጫ ከአቃቂ ወንዝ ጋር ፍጹም አንድ መሆኑ ነው።የአቃቂ ወንዝ ከሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ ከጎጃም በር አካባቢ ካለው ከእንጦጦ ተራራ ተንስቶ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ይፈሳል። ፍራ ማውሮ ካርታ ላይ የተመለከተው ወንዝ ከበረራ በቅርብ ርቀት ጀምሮ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ይፈሳል። የዱከም ወንዝ የፍሰት አቅጣጫ ግን ካርታው ላይ ካለው ዱከም ከተባለው ወንዝ ጋር ፍጹም ተጻራሪ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የበረራን መገኛ ከጎጃም በር በስተ ምስራቅ እንጦጦ ራጉኤል አካባቢ ያደርገዋል።[58] እንጦጦ ራጉኤል አካባቢ የተገኘው ባለ 12 ማማ ታላቅ የመከላከያ ግንብ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዙሪያ የተገኙት የቤተ ክርስትያን ፍርስራሾች ፤ ስትራቴጂያዊ ከፍታ መሬቶች ላይ የተሰሩ የመመልከቻ ማማ ያሏቸው የመከላከያ ግንቦች ወይም ምሽጎች በረራ በእርግጠኝነት ያሁኗ አዲስ አበባ ናት የሚለውን መደምደሚያ ያጠናክራል።**

[58] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped," 4-5.

## የበረራው (የእንጦጦው) የፔንታገን የመከላከያ ግንብ

ከዚህ ቀጥሎ የሰፈረው ዝርዝር የበረራን ታሪክ ከሚከታተለው የማርኮ ቪጋኖ የቅርብ ስራዎች ላይ ተመስርቶ የተጻፈነው። በቅርብ ጊዜ በሰሜን አዲስ አበባ 35 ሄክታር ስፋት ያለው የተንጣለለ ከተማ መገኘቱ ይፋ ሆኗል። ይህ ከተማ ዋሻ ሚካኤል ከሚባለው የድንጋይ ውቅር ቤተ ክርስትያን ጀምሮ እስከ እንጦጦ ማርያም ድርስ ያለውን ቦታ ይሸፍናል። ከተማው በረራ ስለመሆኑ አያጠራጥርም። በዚሁ የቀድሞ ከተማ ውስጥ የፔንታገን ቅርጽ ያለው በዙርያው 12 የመመልክቻ ማማወች (**towers**) ያለው እንደ መከላከያ ግንብ (fortress) የሚያገለግል ቤተ መንግስት ተገኝቷል። ግንቡ ያረፈው በአንድ ሄክታር መሬት ሲሆን ስፋቱም ከጎንደር ቤተመንግስት የላቀ ነው። የመከላከያ ግንቡ በአጠቃላይ 520 ሜትር ርዝመት ባለው ከድንጋይ በተገነባ ውድሞ ወይም አጥር የተከበበ ነው። የውድሞው ከፍታ አንዳንድ ቦታ ላይ እስከ አምስት ሜትር ይደርሳል።[59] የዚህን የመከላከያ ግንብ ውድሞ እና በዙርያው የነበሩትን ማማወች እንዲሁም ውስብስብ የመከላከያ ቁፍሮች (**trench**) በአጼ ምኒልክ ዘመን አንዳንድ የአውሮፓ ዲፕሎማቶች፣ ተጓዦች እና ወታደራዊ ባለሙያዎች ለማየት ችለው ነበር። ከነዚህም ውስጥ ቻርለስ ሚካኤል እና ሲይልቬን ቪኘራስ (Charles Michel and Sylvain Vigneras) የሚባሉ ፈረንሳዊያን እና ሻለቃ ፖዌል ከተን (**Major Powell Cotton**) እና የንጉሳዊ ቤተሰብ አባል የሆነ ኮንት አልበርት ግሌቸን (Count Albert Gleichen) የተባሉ እንግሊዛውያን ይገኙበታል። በተጨማሪም ቸሳረ ኔራዚኒ (**Cesare Nerazzini**) ከምኒልክ መኖሪያ ወደ ጎጃም በር መሄጃ የመከላከያ ግንብ ማየቱን ጽፏል። ሁሉም ግንቡን ያዩት ከአድዋ ጦርነት በኋላ ባሉት አስርት አመታት አጼ ምኒልክ መቀመጫቸውን ከእንጦጦ ወደ አዲስ አበባ ካዛወሩ በኋላ ነው።የመከላከያ ግንቡ ግርማ ሞገስ የሁሉንም ትኩረት ለመሳብ ችሎ ነበር።[60]

ቻርለስ ሚካኤል እና ሲይልቬን ቪኘራስ ግንቡን ፎቶ አንስተውት ነበር። ፎቶው በስተ ምዕራብ በኩል የነበረውን ከ12ቱ ማማዎች በተለየ ግዙፍ የነበረውን ግን ዛሬ በቦታው

---

[59] Marco Vigano, "The Missing Tower At the Entoto Royal Citadel, in three photographs from 1897," 8-25 (file:///C:/Users/Owner/Downloads/The_Missing_Tower_At_the_Entoto_Royal_Ci%20(1).pdf accessed on July 31, 2017); *idem,* "The Names Lost, the Map Grasped," 5-14; and Philip Briggs, *Ethiopia: Bradt Travel Guides* 7th edition (Bradt Travel Guides, 2015), 49–50

[60] Vigano, "The Missing Tower At the Entoto Royal Citadel, in three photographs from 1897", 8-25 (https://www.academia.edu/30552555/The_Missing_Tower_At_the_Entoto_Royal_Citadel_in_three_photographs_from_1897); Count Albert Gleichen, *With the mission to Menelik* (London, 1898), 210-211; and Powell Cotton, *A sporting trip through Abyssina* (Kessinger, 1902, reprint in 2009), 564.

**የማይገኘውን ያሳያል። የፔንታገኑ ምዕራባዊ ክፍል ድንጋይ አንድ ባንድ ተነስቶ ሆን ተብሎ ፈርሷል። በትላልቅ ጥርብ ድንጋዮች ላይ የተቀረጹት ምስሎች ጉዳት ደርሶባቸዋል።በዚህም ምክንያት አዲስ አበባ ብሎም ኢትዮጵያ አስደናቂ ቅርሷን አጥታለች ፤ እያጣችም ነው።[61] ሻለቃ ከተን በዘመናዊ ከባድ የጦር መሳሪያ ካልሆነ በቀረ የመከለከያ ግንቡ በሌላ በምንም ሊደፈር እንደማይቻል አስተያየት ሰጥቷል።[62] ኮንት አልበርት ግሌቸን ወታደራዊ ባለሙያ ስለሆነ ሰለ መከላከያ ግንቡ የሰጠውን ሙያዊ አስተያየት በቀጥታ መጥቀሱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፦**

> Of the old capital of Entotto only a few huts are left, beside the ruins of what must have been an exceedingly strong fortress. Some broken walls are still in existence, and the remains of a large round stone tower dominate the height; but the most extraordinary portion of the fortress is the deep ditch cut in the solid rock. Quite 12 feet deep and 18 feet broad is it; the labour of hewing it out must have been immense, for the rock is not a soft one, and infinite labour of slaves or prisoners must have been spent in its construction. The ditch almost surrounds the fortress and must have formed a complete defence in itself, beside the two parapets, one above the other, which command it throughout.

**ትርጉም**

**ከቀድሞው ከተማ ከእንጦጦ አሁን የቀሩት ጥቂት የጎጆ ቤቶች እና አንድ በጣም ሲበዛ ጠንካራ የነበረ የመከላከያ ግንብ ፍራሽ ነው።አልፎ አልፎ የተናደ ውድሞ እና አካባቢውን እይታ ውስጥ የሚያስገባ ክብ ቅርጽ ያለው የድንጋይ ማማ አሁንም አለ። ከሁሉም አስደናቂ የሆነው የመከላከያ ግንቡ አካል ግን አለቱን በመፈልፈል የተሰራው ጥልቅ ቁፍር ነው። ቁፍሩ ጥልቀቱ 12 ጫማ ስፋቱ ደግሞ 18 ጫማ ነው። አለቱ ልስልስ ስላልሆነ ፈልፍሎ ለማውጣት እጅግ ብዙ ጉልበት የፈጀ መሆን አለበት፤ ለቁፍሩ ግንባታ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የባርያዎች ወይም የጦር ምርኮኞች ጉልበት የፈሰሰበት መሆን አለበት። ቁፍሩ የመከላከያ ግንቡን ዙሪያ በሙሉ ሊባል በሚቻል ስለሚያካብብ በራሱ ሙሉ መከላከያ ነው፤ ይኸውም ከሁለቱ አንዱ ባንዱ ላይ ተደራርበው ከተሰሩት በመከላከያ ግንቡ በዙርያው ከተሰሩት ውድሞዎች በተጨማሪ ነው።" [63]**

**በቅርብ ጊዜ ደግሞ ከላይ ያገኘነው እንግሊዛዊው አርኬዎሎጅስት ዴቪድ ፊሊፕሰን (David Phillipson) እና አንድ ስፔናዊ አርኬዎሎጅስት ስለእንጦጦው ፔንታገን የመከላከያ ግንብ አሰራር ሙያዊ አስተያየት ሰጥተዋል። የመከላከያ ግንቡ ከ1550 ዓመተ ምህረት በፊት የነበረውን የአይቤሪያ ማለትም የፖርቱጋል እና የስፔን የመከላከያ ግምብ የአሰራር ዘዴ ተከትሎ የተሰራ እንደሆነ አረጋግጠዋል። ሳሙኤል ወከር በግንቡ አካባቢ የተገኙት ስብርባሪ የሴራሚክ ውጤቶች**

[61] Vigano, "The Missing Tower At the Entoto Royal Citadel, in three photographs from 1897," 10-11.
[62] Powell Cotton, *A sporting trip through Abyssina,* 564.
[63] Count Gleichen, *With the mission to Menelik*, 210-211; Also quoted in Vigano, "The Missing Tower At the Entoto Royal Citadel, in three photographs from 1897," 7.

ቢያንስ የ400 ዓመት እድሜ እንዳላቸው አረጋግጧል። ከእንጦጦው ፔንታገን የመከላከያ ግንብ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዙርያ 7 ተመሳሳይ የመከላከያ ግንቦች በቅርቡ ተገኝተዋል።[64]

የእንጦጦው ፔንታገን መከላከያ ግንብ ማን እንዳሰራው ምንም አይነት መረጃ አልተገኘም። ምንአልባት አሁን ያለው ግንብ ሆን ተብሎ ካልተደመሰሰ የከርሰ ምድር ባለሙያዎች በቁፋሮ ስለ ግንቡ አሰራር እና ሰለተሰራበት ዘመን የማያወላዳ መልስ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ እስከሚሆን ድረስ ሰለግንቡ አሰርራርም ሆነ ስለአሰራው ንጉስ የሚሰጠው ማንኛውም አስተያይት ከመላምት የዘለለ ሊሆን አይችልም። በኋላ በዝርዝር እንድምናየው አጼ ምኒልክ ወደ እንጦጦ የሄዱበት ዋናው ምክንያት የአጼ ዳዊት አሮጌው ከተማ የሚገኝበት ቦታ መሆኑን ስላመኑ እና ፔንታገኑ የአጼው ቤተ መንግስት ስለመሰላቸው ነው። ይህ በአፍ ቃል ታሪክ የሚነገረው ነው።[65] የፍራ ማውሮ ካርታ በረራ ላይ የእንጦጦውን ፔንታገን የሚያሀል ግዙፍ ቤተ መንግስት አያሳይም። እነ አባ ቶማስም ከላይ እንዳየነው በረራ የንጉሱ ከተማ መሆኑን ከመናገር ውጭ ፔንታገኑን የመሰለ ግዙፍ ቤተመንግስት እንዳለ ለዞርዚ አልነገሩትም። ይህ ፔንታገኑ እነ አባቶማስ በምናኔ ወደ ኢየሩሳሌም ከሄዱ በኋላ የተሰራ ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነው። ስለዚህ የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ አባት የሆኑት አጼ ዳዊት በረራን ቢመሰርቱም ፔንታገኑን ያሰሩት አይመስልም። ማርኮ ቪጋኖ ግንቡን ያሰሩት አጼ ልብነ ድንግል ሊሆኑ ይችላሉ የሚል አስተያየት ሰጥቷል። ምንም እንኳን መረጃ ባይኖረውም ይህ አሰትያየት ለእውነቱ ይቀርባል ብለን እናምናለን።[66] አጼ ልብነ ድንግል ቢያንስ ሶስት ስም ነበራቸው። አንደኛው ዳዊት ነው። ስለዚህ የዳዊት ከተማ የተባለው የእርሳቸውን ሊሆን ይችላል። ፔንታገኑን ማንም ያሰራው ያሁኑ አዲስ አበባ በሰለሞናውያን ዘመን ቅልጥ ያለ ከተማ የነበረ ለመሆኑ እና የከተማውም ስም በረራ እንደነበረ ምንም ጥርጥር የለውም። ከላይ የቀረበው ማስረጃ በረራ ያሁኑ አዲስ አበባ እንደሆነ ለማረጋገጥ በቂ ነው። ከበረራ በአጭር ርቀት ይገኝ ስለነበረው ባደቄ ስለተባለው ከተማ ያሉትን የታሪክ ማስረጃዎችና የምሁራንን አስተያየት ማቅረብ አልቻልንም። በተጨማሪም መረጃው ከበረራ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ከእዚህ ጽሁፍ ታሪኩን ትተነዋል።

[64] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped," 11.
[65] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped," 11-12.
[66] Vigano, "The Names Lost, the Map Grasped," 11-12.

## የበረራ የጨለማ ዘመን ከሽምብራ ኩሬ እስከ አዲስ አበባ መመስረት

**ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት በኋላ ልብነ ድንግል ዳግመኛ ብዙ ሰራዊት ማደራጀት አልቻሉም። ከላይ እንዳየነው አረብ ፈቂህ በረራ እና በአካባቢው ያሉት አድባራት እና የንጉሱ የአጼ ልብነ ድንግል ቤተ መንግስት ከተዘረፉ በኋላ መቃጠላቸውን በዝርዝር ጽፎታል። ይህ የሆነው ደግሞ በ1530 ዓመተ ምህረት ነው። ከ1531 በኋላ ግራኝ ወደሸዋም ሆነ ወደ ዳሞት እና ጋፋት አልተመለሰም። ግራኝ ሙጃሂድ የተባለውን ታማኙን ወረብን እንዲያስተዳድር ሾመው። የወረብ ሰዎችም አዲሱን አስተዳደር ያለውድ በግድ ተቀበሉት። በእስላም መንግስት ለሚተዳደሩ ክርስትያኖች የሚከፈለውን በአረብኛ ጂዝያ (jizya) የሚባለውን የዓመት ግብር ለመክፈል ከሙጃሂድ ጋር ተስማሙ።[67] ሙጃሂድ ወረብን በረራ ላይ ሆኖ ያስተዳድር ወይም ሌላ ቦታ ሆኖ ያስተዳድር እሚታወቅ ነገር የለም። የከተማው ሰዎች ይበተኑ ወይም አይበተኑ ማወቅ አተቻለም። ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት በኋላ ስለበረራ ምንም አይነት የጽሁፍ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም። የጨለማ ዘመን ያልንበትም ምክንያት ይህ ነው።**

**አጼ ልብነ ድንግል ከሽምብራ ኩሬ ጦርነት ጀምሮ በገዛ አገራቸው ስደተኛ ሆነው ነፍሳቸውን ለማትረፍ ካንዱ አውራጃ ወደሌላው አውራጃ እየተዘዋወሩ የወከባ ኑሮ ኖረው በ1540 ዓመተ ምህረት አርፈው በደብረ ዳሞ ተቀበሩ። ልጃቸው አጼ ገላውዴዎስ (1540-1559) ከፖርቱጋል ጥቂት ወታደሮች ጋር በመሆን ግራኝን ደምብያ ወይናደጋ ከሚባል ቦታ ላይ ጦርነት ገጥመው ገደሉት፤ ሰራዊቱም ተበተነ።[68] አጼ ገላውዴዎስ በፈጠጋር፣ በወረብ፣ በሸዋ እና በዳሞት የተቃጠሉትን አድባራት እንደገና አሰርተዋቸው ነበር። በረራና ባደቄ የፈረሱትን ቤተ መንግስቶች እንደገና ለመስራት ሙከራ ያደረጉ አይመስልም። እንዲያውም ንጉሱ ወደ በረራ ጭራሹን የመጡ አይመስልም። ቢመጡ ኖሮ ታሪከ ነገስታቸው በረራንም ሆነ ወረብን በስም ይጠቅሳቸው ነበር። አጼው ሁለት ቤተ መንግስት ነበራቸው። አንዱ በወጅ አውራጃ ዝዋይ ሃይቅ አካባቢ ሲገኝ ሌላው ደግሞ በደዋሮ አውራጃ ልዩ ስሙ አግራሮሃ በሚባል ቦታ ይገኝ እንደነበረ የንጉሱ ዜና መዋዕል ያስረዳል። ደዋሮ በአሁኑ ምስራቅ አርሲ እና ምዕራብ ሀረርጌ አካባቢ የሚገኝ አውራጃ ነበር (ካርታ 2ን ይመልከቱ)። ታሪከ ነግስቱ ላይ የሰፈረውን ቀጥለን ጠቀሰናል፦**

---

[67] Šihāb ad-Dīn, *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia,* 329.
[68] Conzelman, *Chronique de Galâwdêwos (Claudius) Roi d'Éthiopie,* 25-26.

**ወበእንተ አስተጋብኦቶሙ ለዝርዋን ወአርጎቦቶሙ ለስዱዳን ወለአስተላጽቆቶሙ ገብረ መዲና ውስተ አሀቲ ሀገር እም አህጉራተ ወጅ። ወኃደገ ልማዶሙ ለነገሥተ ኢትዮጵያ ዘየዐውዱ እም ብሔር ብሔረ እስከ ስዓተ ንዋም። ዘኢየኃልቅ ወእስከ ዕለተ ድቃስ ዘለዓለም። ወሐነጸ ውስተ ይእቲ አሀቲ ሀገር ማህፈደ ልዑለ ወሠናየ ዘልኩእ ውስቴቱ መልክዐ ወርቅ ወብሩር ወንቡር ውስተ ርእሰ ማእዘንቱ እብን ክቡር ዘእብነ ርካም።**

**ትርጉም**

**የተሰደዱት እና ከሀብት ንብረታቸው በሀይል የተፈናቀሉት በአንድ ቦታ እንዲሰባሰቡ ወጅ ውስጥ በምትገኝ በአንድ ቦታ ከተማ ቆረቆረ። የኢትዮጵያ ነገስታት እስከለተ ሞታቸው፤እስከ ዘላለማዊ እረፍትታቸው ድረስ ከአንዱ አገር ወደ ሌላው አገር ያለማቋረጥ የሚያደርጉትን የጉዞ ልማድ [ከአንድ ከተማ በመርጋት] ተው። በዚህም ከተማ ረጅም እና ድንቅ የሆነ የመመልከቻ ማማ ሰራ ውስጡም በወርቅና በብር የተለበጠ ነው ከማዕዘኑም ላይ የከበረ የእብነ በረድ ድንጋይ ተቀምጧል።[69]**

**ወንጉሥ ገላውዴዎስ ላዕሌሁ ሰላም ሀነጸ መንበሮ በአሐቲ ምድር እምድረ ደዋሮ ወረሰየ ጽርሐ መንግስቱ አግራሮሃ ወእምይእቲ ምድር ቡርክት ተካፈለ ኩላ አህጉራተ ኢትዮጵያ ብዕለ ወተድላ። ወነሥ አምኔሃ ሞገሰ ተሀንጸ አብያተ ክርስትያናት ምዝቡራን ወመራሁታን ይእቲ ለእለ ተዓፅዋ።**

**ትርጉም**

**ንጉስ ገላውዴዎስ ሰላም ብለው ይሁን መቀመጫውን በአንድ በደዋሮ ምድር መሰረተ:: ቤተ መንግስቱንም በአግራሮሃ ሰራ፤ ከዚችም ከተባረከች ምድር ሁሉም የኢትዮጵያ አህጉሮች (አውራጃወች) ክብር እና ተድላ ይካፈላሉ። በዚህም የተመዘበሩትን እና የወደሙትን አብያተ ክርስትያናትን እንደገና ለመስራት የተዘጉትን ለመክፈት ሞገስን አገኘ።[70]**

**ከላይ ያለው መረጃ እንደሚያሳየው አጼ ገላውዴዎስ ትኩረት ያደረጉት ከበረራ በርቀት ወደሚገኙት አካባቢዎች ነው። ወጅም ሆነ ደዋሮ ድንበር ላይ የሚገኙ አውራጃዎች ናቸው። የንጉሱ የቦታ ምርጫ ከጸጥታ ጋር የተገናኘ ሊሆን ይችላል። ደዋሮ ለሀረር እና ለባሌ ቅርብ ነው። ግራኝ ቢገደልም የአዳሎች ሃይል ጨርሶ አልተዳከመም የጸጥታው ሁኔታም አስተማማኝ አልነብረም። ብዙም ሳይቆዩ አጼ ገላውዴዎስ ኑር ከሚባል ከአዳሉ ሱልጣን ኑር ጋር ሲዋጉ በ1559 ሞቱ።[71] ይህ**

[69] Conzelman, *Chronique de Galâwdêwos (Claudius) Roi d'Éthiopie*, 33.
[70] Conzelman, *Chronique de Galâwdêwos (Claudius) Roi d'Éthiopie,* 47.
[71] Conzelman, *Chronique de Galâwdêwos (Claudius) Roi d'Éthiopie,* 101-103.

**በእንዲህ እንዳለ በባሌ አውራጃ በኩል አዲስ የጸጥታ ችግር ተፈጠረ። ይኸውም የኦሮሞ ፍልሰት ነበር።[72]**

**የኦሮሞ ፍልሰት የኢትዮጵያን ፖለቲካ፣ የህዝብ ስብጥር እና አስተዳደር ከግራኝ በበለጠ ሁኔታ እና በዘላቂነት ቀይሮታል። በሰሎሞናዊያን ዘመን የአገሪቱ የሀይማኖት፣ የኢኮኖሚ፣ የባህል፣ የአስተዳደር እና የህዝብ ማዕከል የነበሩ ቁልፍ ቁልፍ አውራጃዎች በኦሮሞ ቁጥጥር ስር ዋሉ። ከነዚህም ባሌ፣ ፈጠጋር፣ ዳሞት፣ ወረብ፣ ጋፋት፣ ወጅ እና ሸዋ ይገኙበታል። ቤተ አምሀራ የሚባለው አውራጃ ሳይቀር ወሎ ፣ ቦረና እና ውጫሌ የሚባሉ የኦሮሞ ጎሳዎች ወረራ አካሄዱበት።[73] በዚህም ምክንያት የአጼ ገላውዴዎስ የወንድም ልጅ አጼ ሰርጸ ድንግል (1563-1596) የመንግስታቸውን መቀመጫ ከሸዋ እና ከጋፋት አንጻራዊ ሰላም ወዳለበት ወደ በጌምድር አዛወሩት።[74] ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሸዋ ፣ የጋፋት ፣ የዳሞት ፣ የጉራጌ እና የሌሎችም አውራጃ ህዝቦች ከማእከላዊው መንግስት ጋር ያላቸው ግንኙነት እየላላ ሄደ። የዳሞት ክርስቲያኖች በአጼ ሰርጸ ድንግል ዘመን የጥንት መኖሪያቸውን ትተው የተሻለ ሰላም ወዳለበት ወደ ጎጃም ተሻግረው ሰፈሩ። አዲሱን መኖሪያቸውን በጥንቱ መኖርያቸው ስም ዳሞት አሉት።[75] የኦሮሞን የፍልሰት ታሪክ የጻፉት በዘመኑ የነበሩት ከላይ የገኘናቸው አባ ባህርይ የተባሉ መነኩሴ ይንን ሁኔታ እንደሚከተለው ይገልጹታል፣ "ወሙልአታ ዘቦረን አጽሐቦሙ ለክርስትያን ዘዳሞት ወዘረዎሙ ወአጥፍአ ሀገሮሙ። ወኮኑ በድወ በዘመኑ ምድረ ሸዋ ወዳሞት።" ይህ ማለት "የቦረን ሙልአታም የዳሞትን ክርስቲያኖች አዳከማቸው ፣ በታተናቸው፣ አገራቸውንም አጠፋው። በሱ ዘመን ሸዋ እና ዳሞት ምድረ በዳ ሆኑ።"[76] አባ ባህርይ የጻፉት አብዛኛው በአይናቸው ያዩትን ነው። ጋሞ ውስጥ**

---

[72] Merid Wolde Aregay, "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508–1708, with Special References to the Galla Migrations and Their Consequences" (Unpublished doctoral thesis, University of London, 1971), chapters 3-5.

[73] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," 281-319. The best work on Oromo migration remains Mohammed Hassen, *The Oromo of Ethiopia: A history 1570-1860* (Cambridge: Cambridge University Press, 1990).

[74] *YaAse Sarsa Dengel Zena Mewa'el BaGeez Ena BaAmarigna*, Baqeres Tenantena Tebeqa baleseltan Yeqers Mermer ena Docmentation Mameriya (Addis Ababa: 1999), 83. This text is also translated into Italian from Geez as *Historia regis Sarsa Denegel (Malak Sagad) accredit Historia Gentis Galla, curante I.Guidi*, edited by Carlo Conti Rossini, Coprus Scriptorum Christianorum Orientalium, Scriptores Aethiopici, Series Altera, 3 (Paris, 1907).

[75] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie (XIIIe-XXe siècles)," 281-319.

[76] Getatchew Haile, ed, *Yeabba Bahriy Dirsetoch,* 71 and 89. This same work is translated as Beckingham, Charles F., and G. W. B. Huntingford (eds.), *Some Records of Ethiopia 1593-1646 Being Extracts from The*

**የምትገኘው እርሳቸው የነበሩባት የብርብር ማሪያም ቤተክርስትን፣ እርሳቸውም የሰበሰቡት የግልንብረታቸው (መጻህፍቶቻቸውን ለማለት ይመስላል) በኦሮሞዎች እንደተዘረፈባቸው፣ ከሞት አፋፍ ደርሰው እግዚአብሄር እንደጠበቃቸው በዚህም ምክንያት ገዳማቸውን ትተው በዘመኑ ከነበሩት ከአጼ ሰርፀ ድንግል (1563-1596) እንደተጠጉ በመጻህፎቻቸው አስፍረውታል።[77] ከሞት የተረፉት ጋፋቶችም የዳሞት ክርስትያኖችን ፈለግ በመከተል የጥንት ርስታቸውን ተትው አባይን ተሻግረው በአዲሱ ዳሞት፣ በደቡብ እና በምስራቅ ጎጃም ሰፈሩ። ወደሰሜን ሸዋ እና ወደ ጉራጌ አገርም ብዙዎች እንደተሰደዱ መረጃ አለ። ጎጃምም ይሁን ሰሜን ሸዋ የሰፈሩት ጋፋቶች የራሳቸውን ቋንቋ ረስተው አማርኛ ተናጋሪ ሆነዋል። ጋፋትኛ ቋንቋ የሚችሉ በጣም ጥቂት ሰዎች እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት በጎጃም ልዩ ስሙ ዳጉሳ ወምበርማ ከሚባል ቦታ ይኖሩ ነበር።[78]**

**ይህ ሁሉ ሲሆን የቀድሞዋ በረራ ከተማ ኗሪዎች እጣ ፈንታ ምን እንደሆነ በግልጽ አይታወቅም። በረራ በከተማነት ትቀጥል ወይም አትቀጥል ለመረዳት አልቻልንም። እንዲሁም የክርስትና ሃይማኖት እና ባህል ከቦታው ሙሉ በሙሉ ይጥፋ ወይም አይጥፋ መረጃ ማግኘት አልተቻለም። በእርግጠኝነት የሚታወቀው በበረራ እና በዙርያዋ የተለያዩ የኦሮሞ ጎሳዎች እንደሰፈሩበት ነው። ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ ቆይቶ የተጻፈው ድርሳነ ራጉኤል የክርስትና ሀይማኖት ከቦታው እንደጠፋ የሚስረዳ መረጃ አስፍሯል። ይህ ድርሳን ስለ እንጦጦ ታሪክ በተለይም በቦታው ሰለሚገኘው የራጉኤል የታቦት ታሪክ ያስረዳል። ስለበረራ ታሪክ የመረጃ ክፍተቱን በመጠኑም ስለሚሞላ ቀጥሎ ያለውን ለአንባቢ ቃል በቃል ገልብጠነዋል፦**

> **ወለእቱሂ አኅወ ዝንቱ ንጉሥ ዘስሙ ያ ዘነገርኩ ቀዲሙ ዜና ሚስጥሩ አንገሣ አምላክ። ለእመኮነ ምኲናኑ ከመ አቡከ ይከውን አምሳለ አበዊከ ነገሥተ ጽድቅ ወይነውኀ መዋዕሊሁ ወውሉደ ውሉዱ ይነግሱ እስከ ኀልቀተ አለም። ወእመ ኮነ ከማከ ኢይነግሥ መዋዕለ አላ ይነብር ነጊሶ ምስለ ውሉዱ 40 ዓመተ ውስተ ሀገረ እዘሀለወት በአንጻረ ምእራቢሀ ለደብረ የረር ከተማ ጽድቁ ለዳግማዊ ዳዊት ዘትሰመይ አምባ ማርያም ለስመ ዛቲ ሀገር ብሂልየ ዘነገርኩከ ቀዲሙ እ ወለእመ ኮኑ ደቂቁ ከማከ እስመ ዛቲ ሀገር ቅድስት ሀገረ መቅደሳ ለእመ እግዚአ ኵሉ ወቅዱስ ወይሬስያ አምላክነ ሐቅለ አናብስት ወአናምርት እስከ 250 አመት ከመ ኢይርኲስዋ ካህናተ ሀሰት በአምልኮ ባዕድ ወበስታየ ጢሰ ዕጸ ዘተረኲሰ በኅበ ካህናቲሁ ለናዖድ ንጉሥ ርቱዓ ኀይማኖት። ወአነ አአቅባ ለዛቲ ሀገር በዘመነ አረማውያን እስከ የሐልፍ 250 ዓመተ አረሚ ወተንባላት ከመ ኢይባው**

*History of High Ethiopia or Abassia by Manoel de Almeida Together with Bahrey's History of the Galla* (London: Hakluyt Society, 1954)

[77] Getatchew, *Yeabba Bahriy Dirsetoch,* 35-41.

[78] Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," 337-369.

**ወኢይንበሩ ዲቤሃ። ወከመዝ እንዘ ይነግሮ ቅዱስ ራጉኤል መልአክ ኮነ ጽባሕ ወተሰበረ እምኔሁ ወተኃጥአ በቱ ራእዩ እንዘ ይሰምዕ ግርማ ቃሉ አኮኑ ደንገጸ ልቦናሁ። [...]**

**ወደቂቀ ያ ይሰደዱ ምድረ እናርእት ወመንፈቆሙ ሀገረ ጉራጌ ተመቲሮሙ በዘመነ መንሱት እምውሉደ ሚ እንዘ የሐውሩ በስደተ ሀገር ጐ ወይነብሩ ማዕከለ አረሚ እንዘ ይሃዝኑ በእንተ ጥፍአተ ክርስትና እስመ ኢይተረከቡ በዘመኖሙ ቀሳውስት ዘ እንበለ አሀደ አሀደ በበሀገሮሙ ለስምዕ ባሕቱ ይተርፉ ውስተ ሀገረ መንዝሀ ወመልዛ በወግዳ ወበጽሕጋ ተኃቤኦሙ ውስተ ጾላእት ወግበበ ሀገር ታሕተ ጸድፍ ወደሴተ ባህር።**

**ትርጉም**

**ስሙ ያ(ዕቆብ) የሚባለው የንጉሱን (የልብነ ድንግልን) ወንድም በሚመለከት ሚስጥሩን ቀደሞ እንደነገርኩህ እግዚአብሄር ያነግሰዋል። የመንግሥቱ አስተዳደር እንደ አባትህ (አጼ ናዖድን ነው) ዘመን ከሆነ ለጽድቅ ነገስታት ለአባቶች እንደሆነው ለእርሱ ይሆናል፤ እድሜውም ይረዝማል ልጆቹም እስካ አለም ፍጻሜ ይነግሳሉ። ነገር ግን ያንተን ከመሰለ እርሱ እና ልጆቹ ከየረር በስተምዕራብ በኩል በምትገኝ የዳግማዊ ዳዊት የፍትህ ከተማ በሆነች አምባ ማርያም በምትባል ቦታ ለአርባ አመት ይነግሳሉ፤ የዚህን ሀገር ስም ቀደም እ(ንጦጦ) ብየ የነገርኩህ ነው። ልጆቹ እንደ አንተ ከሆኑ እግዚ አብሄር ይችን ቅድስት ሀገር ባዕድ አምልኮ እንዳይፈጸምባት፣ ሀሰተኛ ካህናት እንዳያረክሷት፣ ኅይማኖቱ ቀጥተኛ በሆነው በናኦድ ካህናት የተከለከለ ጢስ እንዳይጨስባት ለ250 ዓመት የአንበሳ እና የነብር መዋያ ያደርጋታል። [...] ይህችን አገር (እንጦጦን) በአረማውያን ዘመን ክርስቲያን ያልሆኑ ሰወች እንዳይሰፍሩባት ለ250 ዘመን እስኪያልፍ እኔ እጠብቃትታሁ። ቅዱስ ራጉኤል መልአኩ ይኽንን (ለልብነ ድንግል) እየነገረው ሳለ ነጋ (ጎህ ቀደደ)፤ ተሰወረም። ንጉሱም በመልአኩ በቃሉ ግርማ ልቦናው ሳይደነግጽ ራዕዩ አለቀ።**

**የያ(ዕቆብ) ልጆች በጥፋት ዘመን ወደ እናርእት (እናርያ ማለት ነው)፣ ገሚሶቹ ወደ ጉራጌ አገር በስደት ይለያያሉ። የሚ(ናስ) ልጆች ወደ ጐ(ጐት?) ይሰደዳሉ። በአረማውያን መከካል ይኖራሉ፣ በክርስትና ጥፋት ያዝናሉ ምክንያቱም በዘመናቸው ብዙ ቀሳውስት አይኖሩም በየአገሩም በመንዝ፤ በመልዛ (ላኩመልዛ?)፤ በወግዳ እና በጽሕጋም ከአንድ ቄስ በላይ አይኖርም። ክርስትና እንዳይጠፋ ለምስክርነት ቄሶችን በዋሻ፤በገደል እና በደሴት እግዜአብሄር ያስቀምጣቸዋል።**79

**ድርሳነ ራጉኤል የተጻፈ እንጦጦ ያለው የራጉኤል ቤተ ክርስትያን ከተቋቋመ በኋላ ነው። ዘመኑም በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ነው። ድርሳኑ በእንጦጦ ከግራኝ በፊት ራጉኤል የሚባል ቤተ ክርስትያን እንደነበረ ይገልጻል። አዲሱ ራጉኤል ቤተክርስቲያን የተሰራው የድሮውን ቤተክርስትያን መሰረት በማድረግ ነው። ለአጼ ልብነ ድንግል ራጉኤል የተባለው መልአክ በራዕይ የተናገረው በማስመሰል ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ እስከ አጼ ምኒልክ ዘመን ባሉት 250 አመታት**

[79] André Caquot, "L'homélie en l'honneur de l'archange Raguel (Dersāna Rāguēl)," *Annales d'Ethiopie* 2 (1957), 98-99.

በእንጦጦ እና አካባቢው የተከሰተውን የታሪክ ለውጥ ይናገራል። እስካሁን እንዳየነው እንጦጦ የበረራ መገኛ ነው። ስለዚህ በግልጽ በስም ባይጠቀሰም የድርሳኑ ጸሃፊ የሚያትተው ሰለበረራ ነው።ድርሳኑ የእንጦጦ ክርስትያኖች ወደ እናርያና ወደ ጉራጌ ወደ ሌላም አገር እንደተሰደዱና ክርስቲያን ባልሆኑ አህዛቦች መካከል ለመኖር እንደተገደዱ (ይህ እውነት ነው)፣ በክርስትና ሀይማኖት ምትክ በቦታው የባዕድ አምልኮ እንዳይመለክበት እና ቦታው ክርስትና ኃይማኖት እስከሚመለስ እንጦጦ በቅድስና እንደጸና እንዲቆይ መላኩ እንደጠበቀው እና እግዚአብሄርም ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ከቦታው እንዳይሰፍሩ የነብር እና የአንበሳ መዋያ እንዳደረገው ይናገራል። ስለዚህ ክርስትና ሀይማኖት እና የበረራ ከተማነት በግራኝ ጦርነት ማግስት ተቋርጧል ማለት ነው። ድርሳነ ራጉኤል የሚተርከው ድርሳኑ ከመጻፉ ከ250 አመት በፊት ስለተፈጸመ ታሪክ ቢሆንም እውነተኛነቱ አያጠራጥርም።

ክርስትና ቢቋረጥም አብዛኛው አገር ከቁጥጥራቸው ውጭ ቢሆንም የኢትዮጵያ ነገስታት በተለይም የሸዋ መሳፍንት ከግራኝ በፊት የነበሩትን የአገሪቱን ግዛቶች ለማስመለስ ጽኑ አላማ ነበራቸው። ለምሳሌ አጼ አዲያም ሰገድ ኢያሱ (1682-1706) እስከ ጊቤ ወንዝ እስከ እናርያ እንዲሁም ሸዋ ድረስ ያለውን አገር ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በማዕከላዊ መንግስት ቁጥጥር ስር አድርገውት ነበር።[80] ነገር ግን ጎንደር ከተማ የሃይማኖት እና የፖለቲካው ሽኩቻ አጼ ኢያሱ ከሞቱ በኋላ ስለተባበሰ እናርያ እና ሌሎችም አካባቢዎች መልሰው ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ ሆኑ። በአንጻሩ ግን ሸዋ ውስጥ የተሻለ ሰላም ስለነበር የሸዋ መሳፍንት አገር መልሶ የማቅናቱን ስራ ላይ ለማተኮር ቻሉ። ይህ የተጀመረው በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአዲያም ሰገድ ኢያሱ ሸዋን እንዲያስተዳድሩ በተሾሙት በመርዕድ አዝማች ነጋሲ ክርስቶስ ነው። ነጋሲ ክርስቶስ ዘራቸው ከአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ከአቤቶ ያዕቆብ ይመዘዛል። የነጋሲ ክርስቶስ ልጆች እና የልጅ ልጆች አገር መልሶ የማቅናቱን ስራ ያለማቋረጥ ቀጠሉበት። ሂደቱ ግን በጣም ዘገምተኛ ነበር። መልሶ አገር የማቅናቱ ዘመቻ በንጉስ ሳህለ ሥላሴ (1795-1847) ተፋፍሞ ፍጻሜ ያገኘው ከተጀመረ ከ200 ዓመት በኋላ በንጉሱ የልጅ ልጅ በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በተለይም በ1900 ዓመተ ምህረት ነው።[81]

---

[80] Ignazio Guidi, *Annales Iohannes I, Iyyasu I, et Bakaffa* (Paris: Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium, Scriptores AEthiopici, Series Altera, V, 1903), 206-208.
[81] R. H. Kofi Darkwah, *Shewa, Menilek and the Ethiopian Empire 1813-1889* (London: Heinemann, 1975), 6-9 and no.12, 20, 22-35; and Bouanga, "Le Damot dans l'histoire de l'Éthiopie," 369-430.

አጼ ምኒልክ የአያት የቅድመ አያቶቻቸውን ፈለግ በመከተል መዲናቸውን መጀመሪያ በወጨጫ አደረጉ። ወጨጫን የመረጡበት ምክንያት የጥንቱ የአጼ ዳዊት ከተማ የሚገኝበት ትክክለኛ ቦታ መስሏቸው ነው። ነገር ግን የአጼ ዳዊት ከተማ ወጨጫ ስላልተገኘ በሌላም ምክንያት ከወጨጫ ወደ እንጦጦ ለመሄድ ተገደዋል። የንጉሱን ዜና መዋዕል የጻፉት ጸሀፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ይህንን ጉዳይ እንደ ሚከተለው ጽፈዋል፡ "ነገር ግን የአጼ ዳዊት ከተማ የነበረው የቀድሞው አልተገኘምና ይህ እስኪመረመር በወጨጫ ጋራ በፉሪ ቀኝ ከመካከል ከፍ ያለ ለከተማ የሚመች ሥፍራ አይተው ማሰራት ጀመሩ።"[82] ከዚህ ቀጥሎ ከ1881 ጀምሮ ከአሥር ዓመት በላይ አጼ ምኒልክ እንጦጦ እንደከተሙ፤ ቀጥሎም በባለቤታቸው በእቴጌ ጠሐይቱ አማካኝነት መናገሻቸውን ወደ አዲስ አበባ እናዳዛወሩት ጸሀፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ በዝርዝር ጽፈዋል።አጼ ምኒልክ ወደ ወጨጫም ሆነ ወደ እንጦጦ የሄዱበት ምክንያት የ አጼ ዳዊትን ከተማ ፍለጋ ነው።[83] ስለዚህ  አጼ ምኒልክ አዲስ ከተማ አልመሰረቱም። በዚህ ጽሁፍ ከላይ ባቀረብነው ምክንያት የእንጦጦ ከተማነቱ የቆየነው። ስለዚህ ነው የአዲስ አበባ መመስረት የበረራ ዳግም ልደት ነው የምንለው።

አጼ ምኒልክ የኦሮሞች ጎሳዎወች በስማቸው የሰየሟቸውን የጥንት የአማራ፣ የጋፋት እና የዳሞት ስሞችን ወደጥንት ስያሜአቸው አልመለሱም። ፊንፊኔ የሚባል ከተማ በታሪክ አልነበረም። ምኒልክም አንድ ጋት የኦሮሞ ርስት መሬት አልወሰዱም። ከላይ እንዳየነው አዲያም ሰገድ ኢያሱም ሆነ የሸዋ መኳንንት ወደ እናርያ፣ ወደ አሮጌው ዳሞት እና ጋፋት የዘመቱት አዲስ አገር ለማቅናት አይደለም። የጋፋት ዘሮች እና አማሮች ቋንቋቸው ተወልዶ ያደገበትን እና ለብዙ ሺህ አመታት የኖሩበትን አጽመ ርስታቸውን እንደ አዲስ አገር የሚያዩበት ምንም ምክንያት የላቸውም። ድክመታቸው እንዳለ ሁኖ አጼ ምኒልክ ታላቅ መሪ ነበሩ። ምኒልክ የቀድሞ የኢትዮጵያን አውራጃዎች ዳግም ወደ ማዕከላዊ መንግስት ቁጥጥር ሲያስገቡ የኋላ ሰፋሪዎችን አላፈናቀሉም። በተመሳሳይ የታሪክ ሂደት ያለፉት አገሮች ከአጼ ምኒልክ ፍጹም የተለየ እርምጃ ነው የወሰዱት። ለምሳሌ ስፔናውያን የጥንቱን አገራቸውን መልሰው ሲያቀኑ (Reconquista ይሉታል) ከሰሜን አፍሪካ ሄደው ለ800 ዓመታት የኖሩትን የአረብ እና የበርበር ሙስሊሞች በ1492 ዓመተ ምህረት ጠራርገው የሜዲትራንያን ባህርን አሻገረው ነው ያባረሯቸው። እስራኤላውያንም በኋላ

[82] Gabra-Sellase, *Tarika Zaman ZaDagmawi Menilek Negusa-Nagast ZaItyoppya*, 97.
[83] Gabra-Sellase, *Tarika Zaman ZaDagmawi Menilek Negusa-Nagast ZaItyoppya*, 96-98.

**ሰፋሪዎች በፍልስጤማውያን ላይ በ1948 ዓመተ ምህረት ከስፔን ተመሳሳይ እርምጃ ወስደዋል። በኢትዮጵያ ነገስታት አስተዳደራዊ ልማድ ግን ማፈናቀል ፈጽሞ አይታወቅም። ግብር ከከፈለ እና የንጉሡን አስተዳደር ከተቀበለ ማንም በሰላም የመኖር መብቱ የተጠበቀ ነው፤ ከየት ነው የመጣህ ብሎም የሚጠይቀውም የለም። የተጠበቀውን አንድነት ባያመጣም ስፔናውያን ከተከተሉት ፖሊሲ ይልቅ የኢትዮጵያ ነገስታት የወሰዱት እርምጃ ተራማጅ ነው።**

**ይህንን ጽሁፍ በሁለት የማጠቃለያ ነጥቦች እንዝጋው። አንደኛው መግቢያው ላይ እንደተገለጸው ታሪክ የራሱ የሙያ ስነምግባር አለው፤ ሀቀኛ ታሪክን መቀበል ስልጡንነት ነው። ሁላችንም ነጻ እንድንወጣ እና ፍትህ እንዲሰፍን በሙያው ባለቤቶች የተፈተነ እና የታመነበት የታሪክ እውቀት ያስፈልገናል። የታሪክ ተመራማሪዎችም ለሙያው ስነ ምግባር መገዛት አለባቸው። ታሪክን ከፖለቲካ አመለካከት አንጻር መተንተን መቆም አለበት። በተለይ የታሪክ ባለሙያ ያልሆነ ሰው ፍጹም እርግጠኛ ስላልሆነበት ስላለፈው ታሪክ ሲጽፍ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። ብዙ መጽሀፍ ማንበብ በራሱ የታሪክ ባለሙያ አያደርግም። ታሪክን መካድ ፣ ያለሙያ በድፍረት ወይም በድንቁርና መጻፍ ጉዳቱ የከፋ ለመሆኑ የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ጥሩ ማስረጃ ነው። ሁለተኛው ሀቀኛ ታሪክ ጽኑ የአንድነት መሰረት ነው። ፍትህንም ለማስፈን ወሳኝ ሚና አለው። ለፍትህ እና ለአንድነት ሲባል በታሪክ ሂደት ጉዳት የደረሰባቸውን ህዝቦች እውቅና መስጠት ከጉዳታቸው እንዲያገግሙ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ነው (አሜሪካውያን affirmative action ይሉታል)።ታሪካቸውም መዘከር አለበት። ኢትዮጵያ እንደካናዳ ካሉ ስልጡን አገሮች የታሪክ ተመክሮ ብዙ መማር ትችላለች። ለምሳሌ በካናዳ የትምህርት ተቋማት አስተማሪዎች ለተማሪዎቻቸው በሚያዘጋጁት ሲለበስ (syllabus) ተቋማቱ ለሚሰሩበት መሬት የጥንት ባለቤቶች የምስጋና አንቀጽ እንዲያስገቡ የሚያስገድድ ፕሮቶኮል አለ። ለአብነት ያህል የቶሮንቶ ዩንቨርሲቲ የምስጋና አንቀጽ በከፊል እንደሚከተለው ይነበባል፡-**

> The sacred land on which the University of Toronto operates has been a site of human activity for 15,000 years. This land is the territory of the Huron-Wendat and Petun First Nations, the Seneca, and most recently, the Mississaugas of the Credit River. [...]. Today, the meeting place of Toronto is still the home to many indigenous people from across Turtle Island and we are grateful to have the opportunity to work in the community, on this territory.
>
> **ትርጉም**
>
> **የቶርንቶ ዩንቨርሲቲ የሚሰራበት የተቀደሰ መሬት ለ15,000 ዓመታት ሰዎች ኖረውበታል። ይህ መሬት የመጀመሪያዎቹ የነባር ህዝቦች የሁሮን-ዌንደት፣ የሰነካ እና ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ የክሬዲት ወንዝ**

(አካባቢ ኗሪ) የሆኑ የሚሲሿጋሦች ነው። [...] ዛሬም ቶሮንቶ በመገናኛነት የሚያገለግለው መሬት በተርትል አይላንድ ዙሪያ የሚኖሩ የብዙ ተወላጆች አገር ነው፣ እኛም ከማህረሰቡ ጋር በዚህ መሬት ለመስራት እድል ስላገኘን እናመሰግናለን።[84]

ይህ የኋላ የአውሮፓ ሰዎች ካናዳ ሲሰፍሩ በተወላጆች ላይ ለደረሰው ጉዳት እውቅና ለመስጠት እና ለሚኖሩበት መሬት ለጥንቱ ባለርስቶች ምስጋና ለመስጠት ነው።

ወደኢትዮጵያ ስንመለስ የአማራ እና የጉራጌ በተለይም ደግሞ የጋፋት ህዝብ በኋላ ሰፋሪዎች ብዙ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ጋፋትን በተመለከተ ጉዳት ደርሶበታል ብቻ ሳይሆን እንዲጠፋ ተደርጓል። የጋፋት ህዝብ ታላቅ እና በጣም ጥንታዊ ህዝብ ነው። ከጎጃም ውጪ የጋፋት ርስቱ፣ ዘሩ፣ ታሪኩ እና ባህሉ ፈጽሞ ተረስቷል። የጋፋትን ህዝብ ለማመስገን ፣ ለጥንታዊነቱ እና ለታላቅነቱ እውቅና ለመስጠት የኋላ ሰፋሪዎች የቀየሯቸውን ስሞች በጥንቱ ስም እንዲጠሩ ማድረግ የመጀመሪያ እርምጃ ነው። በዚህ መሰረት አዲስ አበባን እና አካባቢውን በረራ፣ በግቤ ወንዝና በአዋሽ ወንዝ መካከል ያለውን አገር ዳሞት፣ በጉደር እና በሙገር ወንዝ መካከል ያለውን በጥንት ስሙ እንደገብጣን ማለት ያስፈልጋል። የኋላ ሰፋሪዎች ለገፏቸው ለነባር ህዝቦች፣ ርስታቸው ለፈለሰባቸው ፣ ቋንቋቸው ለጠፋባቸው እና ዘራቸው ለተደመሰሰባቸው እውቅና መስጠት እና ምስጋና ማቅረብ ስልጡንነት ነው።

ኢትዮጵያ ግን ሲደረግ ያየነው ከካናዳ ተቃራኒ ነው። ርስታቸው የፈለሰባቸው እና ቋንቋቸው የተደመሰሰባቸው ሰዎች ወራሪ ተብለው ዳግም ጉዳት ደርሶባቸዋል። "በፊት የበቀለን ጆሮ በኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠው" እንዲሉ የጋፋት እና የዳሞት ዘሮች ፣ ጉራጌዎች እና አማሮች ቋንቋቸው ተወልዶ ካዳገበት፣ አያቶቻቸውና ቅድመ አያቶቻቸው ትናንት በእየሩሳሌም ከመሰሉት ከጥንት አጽመ ርስታቸው አገራችሁ አይደለም ተብለው ተባረዋል። ለዘላቂ ሰላም እና ፍትህ ሲባል ኢትዮጵያ ከካናዳ መማር አለባት።

ሁላችንንም ባለርስት የሚያደርግ በኢትዮጵያዊ ዜግነት ላይ የተመሰረተ ስርዓት እናልም።

---

[84] Canadian University Acknowledgement of Indigenous Lands, Treaties and Peoples (http://perceptionsofchange.ca/home_htm_files/CRS_Table.pdf, accessed 2 August 2017)

## Bibliography

### Unpublished Sources

Bouanga, Ayda. “Le Damot dans l’histoire de l’Éthiopie (XIIIe-XXe siècles): Recompositions religieuses, politiques & historiographiques.” Paris, PHD dissertation submitted at the University of Paris, 2013.

Wolde Aregay, Merid. “Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508–1708, with Special References to the Galla Migrations and Their Consequences.” Unpublished doctoral thesis, University of London, 1971.

Waqjera, Takla Iyasus, Alaqa. “YaZaman Tarik Mataraqemiya.” Unpublished handwritten text. National Library 382/63. Addis Ababa.

### Published Sources

Baeteman, J. *Dictionnaire Amarigna-Français. Dire-Daoua*. Imprimérie Saint Lazare, 1929.

Beckingham, Charles F., and G. W. B. Huntingford, eds. *Some Records of Ethiopia 1593-1646 Being Extracts from The History of High Ethiopia or Abassia by Manoel de Almeida Together with Bahrey's History of the Galla*. London: Hakluyt Society, 1954.

Bernal, Martin. *Black Athena The Afroasiatic Roots of Classical Civilization* vols 1 and 3. New Brusnwick: Rutgers University Press, 1987 and 2006.

Bernal, Martin. ‘A New Proto-Semitic.” Paper given at the tenth annual North American Conference of Afroasiatic Linguistics. Boston, 1980.

Blecher, Roger. *Language, Archaelogy and the African Past*. Cambridge, AltaMira Press, 2006.

Breternitz, Harwig and Richard Pankhurst. “Barara, the royal city of 15th and early 16th century (Ethiopia): medieval and other early settlements between Wechecha Range and Mt Yerer: results from a recent survey.” *Annales d'Ethiopie* 24 (2009): 209-249.

Briggs, Philip. *Ethiopia: Bradt Travel Guides.* 7th edition. Bradt Travel Guides, 2015.

Bureau, Jacques. “Note sur Les Eglises du Gamo.” *Annales d'Ethiopie* vol. 10 (1976), 295-303.

Caquot, André. “L'homélie en l'honneur de l'archange Raguel (Dersāna Rāguēl).” *Annales d'Ethiopie* 2 (1957): 98-99.

Caquot, André. “Note sur Berber Māryām.” *Annales d'Ethiopie* vol. 1 (1955), 109-116.

Chaillot, Christine. *THe Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Tradition: A brief Introduction to its Life and Spirituality.* Paris: Inter-Orthodox Dialogue, 2002.

Conti Rossini, Carlo. ‘Gadla Anorewos seu acta sancti Honori.’ Louvain, *Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium, Scriptores AEthiopici,* Series Altera, 20, 1905: 1-16.

Conzelman, William. *Chronique de Galâwdêwos (Claudius) Roi d'Éthiopie*, Texte Éthiopien traduit, annoté et précédé d'une Introduction Historique. Paris, 1895.

Cotton, Powell. *A sporting trip through Abyssina.* Kessinger, 1902, reprint in 2009.

Caquot, André. “L'homélie en l'honneur de l'archange Raguel (Dersāna Rāguēl).” *Annales d'Ethiopie* 2 (1957): 98-99.

Crawford, O.G.S. ed. *Ethiopian Itineraries ca. 1400-1524*. Cambridge University Press for the Haklyut Society, 1955.

Darkwah, R. H. Kofi. *Shewa, Menilek and the Ethiopian Empire 1813-1889*. London: Heinemann, 1975.

Dästa Täklä-Wäld. *YäAmarerñña Mäzgäbä Qalat*. Addis Ababa: Artistic Printing press, 1962 Eth. Cal.

Davies, Surekha. “The Wondrous East in the Renaissance Geographical Imagination: Marco Polo, Fra Mauro and Giovanni Battista Ramusio.” *History and Anthropology* 23: 2 (2012): 215-234.

Demeke, Girma A. “The Ethio-Semitic Languages (Re-examining the Classification).” *Journal of Ethiopian Studies* 34: 2 (2001): 59-70.

Demeke, Girma. *The Origin of Amharic*. 2nd ed. Trenton: The Red Sea Press, 2009.

Derat, Marie-Laure. *Le Domaine des rois éthiopiens (1270–1527): espace, pouvoir et monachisme.* Paris: Publications de la Sorbonne, 2003.

*Dersana Urael BeGeezena BeAmaregna: Malka Urael beLeSana Geez*. Addis Ababa. 1985.

Ehret, Christopher. *Reconstructing Proto-Afroasiatic (Proto-Afrasian): Vowels, Tone, Consonants, and Vocabulary.* Los Angeles: University of California, 1995.

Falchetta, Piero. *Fra' Mauro's World Map: With a Commentary and Translations of the Inscriptions*. Turnhout: Brepols Publishers, 2006.

Foot, E. C. *A Galla-English, English-Galla Dictionary*. Cambridge: Cambridge University Press, reprint 1968.

Frajzyngier, Zygmunt and Erin Shay, ed. *The Afroasiatic Languages*. Cambridge: Cambridge University Press, 2012.

Gabra-Sellase, Alaqa, *Tarika Zaman ZaDagmawi Menilek Negusa-Nagast ZaItyoppya*. Addis Ababa: Berhanenna Sälam Printing Press, 1959 Eth. Cal. Translated into French by Maurice de Coppet as *Guèbrè Sellassié: Chronique du Règne du Ménélik II, Roi des Rois d'Éthiopie.* Paris: Maisonneuve Frères, 2 vols., 1930, 1932.

Gleichen, Count. *With the mission to Menelik*. London, 1898.

Gamta, Tilahun. *Comprehensive Oromo-English Dictionary*. Addis Ababa: Karrayyu Publishing, 2004.

Iganzio Guidi, "Le Canzoni Geez-Amarina in onore di re Abissini." *Rendiconti della Reale Accademia dei Lincei*, Series Quarta, V (Roma, 1889), 53-66.

Hable Sellassie, Sergew. *Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270*. Addis Ababa: Haile Sellasie I University, 1972.

Haile, Getatchew, ed. *Yeabba Bahriy Dirsetoch oromochin kemmimmelekketu leloch senedoch gara* [*The Works of Abba Bahriy with Other Documents concerning the Oromo*]. Collegville, 1995.

Hassen, Mohammed. *The Oromo of Ethiopia: A history 1570-1860*. Cambridge: Cambridge University Press, 1990.

Hudson, Grover. "Ethiopian Semitic archaic heterogeneity, Ethiopian Studies at the Millenium." In *Proceedings of the 14th International Conference of Ethiopian Studies*, Baye Yimam et al, eds., 1765-1776. Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies, 2000.

Hudson, Grover. *Northeast African Semitic-Lexical Comparisons and Analysis*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz Verlag, 2013.

Guidi, Ignazio. *Annales Iohannes I, Iyyasu I, et Bakaffa.* Paris: Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium, Scriptores AEthiopici, Series Altera, V, 1903.

Kane, Thomas. *Amharic Dictionary*. Wiesbaden, Harrassowitz, 1990.

Kraf, J. L. *Vocabulary of the Galla Language*. London: Church Missionary Society, 1842.

Kaplan, Steven. *The Monastic Holy Man and the Christianization of Early Solomonic Ethiopia*. Wiesbaden: Coronet, 1984.

Perruchon, Jules. *Les Chroniques de Zar'a Yâ'eqôb et de Ba'eda Mâryâm, Rois d'Éthiopie de 1434 à 1478* (Texte Éthiopien et Traduction), Précédées d'une Introduction. Paris: Émile Bouillon, 1893.

Perruchon, Jules. "Histoire des guerres d'Amda Seyon, roi d'Éthiopie." *Journal Asiatique*, Series 8, XIV (1889).

Phillipson, David. *Foundations of an African Civilisation: Aksum & the northern Horn 1000 BC-AD 1300.* London: James Curry, 2012.

Strachan, Bruce. "Barara: Abyssinia's Lost Mediveal City" (https://cityofbarara.wordpress.com/ accessed on July 31, 2017)

Tamrat, Taddesse. "Ethnic Interaction and Integration In Ethiopian History: The Case of the Gafat." *Journal of Ethiopian Studies* 21 (1988): 121-154.

Tamrat, Taddesse. *Church and State in Ethiopia 1270-1527.* Oxford: The Clarendon Press, 1972.

Tasamma, Kasate Berhan. *YäAmarrenna Mazgaba Qalat*. Addis Ababa, 1951 Eth. Cal.

Tegegne, Habtamu. "The Edict of King Gälawdéwos Against the Illegal Slave Trade in Christians: Ethiopia, 1548." FEATURED SOURCE. *The Medieval Globe* Vol. 2 : No. 2 (2016), 73-114.

Tutschek, Lawrence. *Dictionary of the Galla Language*. Munich, 1845.

Tutschek, Karl. *Lexicon der Galla Sprache*. 1844.

Uṯmān, Šihāb ad-Dīn Aḥmad bin Abd al-Qāder bin Sālem bin. *Futūḥ al-Ḥabaša: The Conquest of Abyssinia, [16th century].* Edited and translated by Paul Stenhouse. Hollywood: Tsehai Publishers, 2003.

Vigano, Marco. "The Names Lost, the Map Grasped Central Shoa on the Fra Mauro map, is significant lost medieval Ethiopia recovered?" A paper for the Act Book of the "Exploring Ancient China's Links to Africa" meetup, Addis Ababa, 2014.

Vigano, Marco. 'Barara, Entoto.' The Advanced Science Center for Heritage Consevration (https://www.academia.edu/9463355/Barara_Entoto._An_advanced_science_centre_for_natural_and_cultural_heritage_conservation accessed on August 1, 2017).

Vigano, Marco. "The Missing Tower at the Entoto Royal Citadel, in three photographs from 1897," 8-25 (file:///C:/Users/Owner/Downloads/The_Missing_Tower_At_the_Entoto_Royal_Ci%20(1).pdf accessed on July 31, 2017).

Walker, Samuel. "The Lost Cities of Ethiopia." Popular Archaelogy 27 (2017) (http://popular-archaeology.com/issue/summer-2017/article/the-lost-cities-of-ethiopia acessed 7/31/2017).

YaAsé Sarsa Dengel Zena Mawa'al Geez Ena Amarenna. Baqers Tenatena Ena Tebaqa Balaseletan YaQers Mermer Enna Ma'ikalawi Documentation Mamriya. Addis Ababa, 1999 Ethio. Cal.; Translated into Italian as *Historia regis Sarsa Denegel (Malak Sagad) accredit Historia Gentis Galla, curante I.Guidi*. Edited and translated by Carlo Conti Rossini. Paris, Coprus Scriptorum Christianorum Orientalium, Scriptores Aethiopici, Series Altera, 3, 1907.

Zär'a Ya'qob. *The Epistle of Humanity of Emperor Zar'a Ya Eqob,* Corp. Script. Christ. Orient., Script. Aeth., vol. 96. Louvain, 1991.

Zär'a Ya'qob. *Mäs'hafä Melad*. Edited by Kurt Wendt as *Das Mashafa Milad (Liber Nativitatis) und Mashafa Sellase (Liber Trinitatis) des Kaisers Zar'a Ya'qob*, Corp. Script. Christ. Orient., Script. Aeth., vols. 41 and 43. Louvain, 1962 and 1963.

Zär'a Ya'qob. *Mäs'hafä Berhan.* Edited and translated by Carlo Conti Rossini and Lanfranco Ricci as *Il Libro della Luce del Negus Zar'a Ya'qob (Mashafa Berhan),* Corp. Script. Christ. Orient., Script. Aeth., vol. I [vols. 47, 48, 51, and 52. Louvain, 1964 and 1965.